

«እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ» ማቴ ፲፫ ፡ ፫

« በለሰለሰው መሬት ላይ የወደቀውም ዘር መልካም ፍሬ አፈራ » ከ፳–፲

# ትንሣኤ



«እግዚአብሔር የፈጠራቸው እንስሳት ሁሉ አዳምን ወደውት ወደ እርሱ ሲመጡ አዳምም ምን ብሎ እንደሚጠራቸው ያውቅ ነበር ።»

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 12 ፲፱፻፹ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና፣ ታሪክ ሥርዓትና ዜና ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐም ለሥራ እንነሳ የሚል ስለሆነ «ትንሣኤ» ተብሎ ተሰይሟል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ ።

በሁለት ወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

አዘጋጅ
ነቅዓ ጥበብ ወንድም

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ ቁ 3137
አዲስ አበባ

ሰኔ ፲፪ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ ም/
ቁጥር ፲፪

# ማ ው ጫ

## አርእስት


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች | ፩ |
| ኃላፊነትን ማወቅ (ርእሰ አንቀጽ) | ፫ |
| የሰበካን ጉባኤ ለማደራጀት | ፬ |
| ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ | ፱ |
| ሃይማኖት በሶሻሊስት አገሮች | ፲፩ |
| «ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም» | ፲፫ |
| ሐቀኛ ሰው ይፈለጋል | ፲፬ |
| «ርእሰ ካህናት» | ፲፮ |
| የሴቶች ድምጽ በመገናኛ ዘዴ | ፲፰ |
| በጅማ ከተማ የተደረገው መንፈሳዊ የጥናት ጉባኤ ተፈጸመ | ፲፱ |
| ሁሉም ድርሻውን ሲያበረክት | ፳፩ |
| በበዓለ ሃምሳ ያሉት ረቡዕና ዓርብ ለምን ይበላሉ ? | ፳፪ |
| የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ይድናል | ፳፫ |
| የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና | ፳፬ |
| የእግዚአብሔር ህላዌ | ፳፮ |
| ልማድ ሃይማኖት አይደለም | » |


# ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በታኅሣሥ ወር ፸ ዓ-ም- ቁጥር ፱ በወጣው ትንሣኤ መጽሔት በጠቅላላ የመጽሔቱ ፤ መልእክት ፤ መከፈቻም ፤ የሚአንጸባርቀው ፩ኛ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከተቋቋመ እስካሁን ያሳለፋቸው ውሳኔዎች በሥራ አለመተርጎሙን ፪/ መልእክቱ ባሁኑ ዓመት የወጣው የጥቅምቱ ሲኖዶስ ያለፈውን ሁሉ ጉድለት ለማሟላት ያቀረበውን መፍትሔ በሥራ ለማንጸባረቅ ከስድስቱ ሊቃነ ጳጳሳት ላይ የተደራረበ ሥራና ሐላፊነት ማቅረብ ነው ።

የራሴን ጭንቀት ከሁሉ ቅድሚያ በመጠኑ እንድታውቁልኝ አሳስባለሁ የምማርበት ት/ቤት የሚሲዮን ክርስቲያን ተከታዮች ት/ቤት ነው ። ሁላችንም የክርስቶስ ቤተሰቦች ነን ቢባልም የእምነታችን ሥነ ሥርዓት በመለያየቱ እልፎ እልፎ መወቃቀስ አይቀርም ። በዚሁ ምክንያት ወጣት ጓደኞቼ በሙሉ የሚሲዮን ክርስቲያን አማኞች በመሆናቸው ብዙ ጥያቄ ስለሚአቀርቡልኝ በሃይማኖቴ በኩል ትክክለኛና አጥጋቢ መልስ በመመለስ ፤ ተቋቁሚአለሁ ኢትዮጵያዊ እንደመሆኔ መጠን ፤ ጠንካራውና የኦርቶዶክስ እምነት ሳይንሳዊ ከሆነው ትንተናው ጋር እምነቱና መጽሐፍ ቅዱስ ልዩነት የማይታይባቸውና ተደጋጋፊነታቸውን በማብራራት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ፍልስፍናን ሳላስደፍር እኔም ሳላፍር እገኛለሁ ።

መጽሔቱ ያቀረባቸው ብፁዓን ጳጳሳት የሥራ ሁኔታ በጣም አደናጋሪ ሁኖብኛል ። እስከዛሬ ድረስ የበላይነቱን አስደፍሬ የማላውቀውን ከተከራካሪነቱ አንድ ነጥብ ዝቅ አድርጎኛል ።

፩/ ስድስቱ ሊቃነ ጳጳሳት የየሀገረ ስብከቱ ባለአደራ ናቸው ። ይህ ከታወቀ በያሉበት ሀ/ ስብከት ውስጥ ብዙ አዳዲስ ሃይማኖቶች በመግባት ሥር ሰደው ኦርቶዶክስ ሃይማኖት በመመንመን ላይ መሆኗን ተከራካሪዎች በተጨባጭ ማስረጃ አቅርበውልኛል ይህም ምእመኑ አስተማሪ ከማጣት የተገኘ ጉድለት ለመሆኑ ይሰማኛል ።

፪/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ እስካሁን ድረስ ከሥራ ላይ አልዋለም ነበር ። ለተባለው ከሥራ ላይ ላለመዋሉ ምክንያት የሆኑት ሌላ ጳጳሳት ሳይሆኑ አሁን ያሉት ጭምር ለመሆናቸው አሻሚ ያልሆነ መረጃ ቀርቦልኛል ፤ የቀረበውን እንዳልጠቁም ፤ ሰፊ ስለሆነ በኔው ብቻ እንዲወሰን አልፈዋለሁ ።

፫/ አዲሱ ዲሞክራቲክ ኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ፤ ሥራን ደራርቦ መያዝና የሥራን መስክ ለሌሎች ጭቁኖች እንዳይዳረሱ የሚደረገውን የተደራረበ የሥራ ሰንሰለት የማጣበብ ዘዴ ታወግዛለች ። ስለዚህ በቂ ትንተና ከጓደኞቼ ቀርቧል ። ነገር ግን መልሴ አጥጋቢ ሆኖ አላገኘሁትም ።

፬/ አሁን ባገራችን ያለው ተጨባጭ የፍልስፍና ልማት ከገጠር ወደ ከተማ እንደመሆኑ መጠን ብፁዓን ጳጳሳት በመደረብ የያዙት ሥልጣን በወንጭፍ የማይሰራ መሆኑ በእርግጥ ይታመናል ። ቤተ ክርስቲያናችንም እራሷን የቻለች ድርጅት እንደመሆኗ በቂ የትምህርት ማስተላለፊያ የላትም ።

፭/ በአሁኑ ጊዜ ዘመናዊውን ሳይንሳዊ የሃይማኖት ፍልስፍና ከጥንታዊው ምሥጢረ ሃይማኖት ፍልስፍና ጋር አጣምረው በማስረዳት የሚጠቅሙ ወጣት ኦርቶዶክሳውያን ምሁራን ሥራ ፈተው በየቦታው ይገኛሉ። በቂ ችሎታ ያላቸው መንፈሳውያን ልጆች የሥራ ያለህ እያሉ ብፁዓን ጳጳሳት ሥራን ደራርቦ ለመሥራት ሥልጣን አገኙ የሚለው አጥጋቢነቱ እስከ ምን ድረስ ነው ? ለሚለው መልስ ለማግኘት ያልዳበስኩት መጽሐፍ የለም ቤተ መጻሕፍት ሂጄ መጽሐፈ መነኮሳት ብመለከት ለብፁዓን የሚያዝላቸው ሥራ አሁን በሲኖዶሱ ከተቀበሉት ውጭ ሆኖ ይታያል ። « ባጠቃላይ የማሳስበው ከዘጠኝና ካሥር ዓመት መካከል ያለሁ ሕፃን እንደመሆኔ መጠን ጽሑፌን በቶሎ ሳይቆራርጡ ያስፍሩልኝ መልስ ከናንተ ለማግኘት ብቻ ክርክሬን ቀን የሰጠሁት ስለሆነ ያንተ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች መልስ እንኳን ለመስጠት አይችሉም በማለት ልጆችእን ዳይጨቀጭቁኝ እፈልጋለሁ።

ሕፃን ዘሩባቤል ዘለቀ ከማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር አዲስ አበባ ።

● ለመጀመሪያው ጥያቄ መልሱ አንተ እንዳልከው ባለአደራ መሆናቸው ግልጽ ነው ። ሆኖም በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ብቻ አመካኝቶ ዝም ማለቱ የሚያዋጣ አይደለምና ሁላችንም ለሃይማኖታችን ቀናተኛ መሆን አለብን።

፪/ በሁለተኛው ጥያቄህ ላይ የደረደርከው ዓረፍተ ነገር ትክክል ነው መረጃ ላቅርብ ብለሃል ምን ዓይነት እንደሆነ ብትገልጸው ደስ ይለን ነበር ። ሆኖም ዛሬስ ምን ያህል በሥራ የተተረጐመ ይመስልሃል ? ገና ለወደፊቱ ይሠራበት ይሆናል ብለን ነው እኛም የምንጠብቀው አንተም በእኛው አሳብ ተስማማ ።



www.ethiopianorthodox.org

፫/ መቼም እኛ እንደሚመስለን ይህ የሥራ ቦታ ማጣበብ አይደለም ምክን ያቱም ሌላ ተጨማሪ ደመወዝ እያገኙበትም እንዲያው በአባትነታቸው ቋሚ ተጠሪ እንዲሆኑ እንጂ ፣ ለእያንዳንዱ መምሪያ ኃላፊ አለውና ነው ። ችግሩ ይህ አልነበረም ኃላፊነቱ ቀላል ስላልሆነ ምን ያህል የሥራ ፍሬ እንደ ሚያሳዩ መመልከቱ በመጨረሻም አስተያየትን መስጠቱ ሳይሻል የሚቀር አይመስለንም ።

፬/ በአራተኛው ተራ ቁጥር የጠየቅከው ጥያቄ ከ፫ተኛው ጥያቄህ ጋር ተመሳሳይ ነው ። ሆኖም ወደመጨረሻው ገደማ አንገብጋቢ ጥያቄ በማቅረብህ ልትመሰገን ይገባሃል ቢሆንም ሰው ባለው መሣሪያ መጠቀም ስላለበት እኛም ለጊዜው በመጽሔታችንና በጋዜጣችን ብንጠቀምባቸው መልካም ነው ።

፭/ በአምስተኛው ተራ ቁጥር ያቀረብከው ጥያቄ እኛ የምንሰጠው መልስ አይደለም ለምን ? ቢባል ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዛባትን ስታስተካክል ታስብበት ይሆናል ። እኛ የምንለው የሥራ ፍሬ ያሳዩ አንተ እንደጠቀስከው ለተማሩት ሰዎች ሥራ ፈጥረው የሥራ ቦታ ይሰጣቸው ፣ ዛሬውኑ በአስተያየትህ ይጠቀሙበት ነው የምንለው ።

* * *

ከሁሉ በፊት የሥላሴ በረከት ጸጋ ቸርነት ከሁላችን ጋር ይሁን እላለሁ። ለረዥም ጊዜ በናፍቆት ስንጠብቀው የነበረውን የመንፈሳዊ መጽሔት ዝግጅት በቅርቡ በማየቴ በመስል ኦርቶዶክሳውያን ወጣት ወንድሞቼና እኅቶቼ ስም ይህች የማበረታቻ መልእክት ትድረሳችሁ ። ምንም እንኳ መጽሔቱን ያገኘሁት ባጋጣሚ ያለፈውን አንድ እትም ብቻ ቢሆንም ሃይማኖታችን በእንደዚህ ያለ የመጽሔት ዝግጅት እንደተደገፈ የመጣ ቢሆን ኖር ይኖር የነበረው ተጨባጭነት ስለሚታየኝ ደጋግሜ ባመሰግናችሁ ደስ ይለኛል ። ቁም ነገሩ መጽሔት አለን ብዬ ለመመካት ብቻ ሳይሆን እትሙ በመጠን እየበዛና በብዙ አንባቢ ምዕመናን እጅ እንዲዳረስ የሚደረጉ ጥረቶች ካሉ ይልቅ የሚያስመኩ ናቸው ። መጽሔቱን በአምዶች በመከፋፈል ከኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች አካባቢ ለሚቀርቡ መንፈሳዊ ውይይቶች ቦታ ቢሰጠው ለዓላማው ከፍተኛ ድርሻ ሊያበረክት መቻሉን በዚህ አጋጣሚ ልጠቅስ እወዳለሁ ። ለጥረታችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን ። እኛም መጽሔቱን ባልተራራቀ ቀናት እናገኘው ዘንድ ምኞታችን ነው ።

ሰሎሞን በላይነህ
አዲስ አበባ

—አቶ ሰሎሞን በላይነህ የእኛም አሳባችን እንደ እርስዎ ነው ። አሁንም ወጣቶች በሚመለከታቸው አግጣጫ እንዲጽፉ መልእክታችንን እናስተላልፋለን ።


## ማሳሰቢያ

፩ኛ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት "ድምፀ ተዋሕዶ" የተሰኘ ጋዜጣ ከአሁን በፊት ለ14 ዓመታት ያህል እያሳተመ ለምእመናን እንዲዳረስ ሲያደርግ ቆይቷል ።

አሁን ግን በይበልጥ ከመስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ጀምሮ በማኅበርተኙንትም ዘንድ በበዓላት ቀን ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚዳረስበትን መንገድ በማጥናት ላይ ስለሆነ ይህንን ማሳሰቢያ የሚያነቡ ሁሉ አስተያየታቸውና ትብብራቸው እንዳይለየው ያሳስባል ።

2ኛ መንፈሳውያን መልእክቶችን መንፈሳውያን የሆኑ ዘመናውያን መዝሙሮች ንና ምንታውያን ዜማዎችን በካሴት እየቀረፀ ካሴት ለማያቀርቡ የካሴት ዋጋ $5 ና የአገልግሎት ደግሞ 2 ብር ብቻ እያስከፈለ የሚሰጥ መሆኑን በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣችን ማሳሰባችን ይታወሳል ።

አሁንም በዚሁ ሁኔታ የቀጠለ መሆኑን እንገልጣለን ።



አድራሻችን አራት ኪሎ ብሔራዊ ሸንጎ ፊት ለፊት
የስልክ ቁጥር 11 - 66 - 15
የፖ.ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ



( ርእሰ አንቀጽ )

# ኃላፊነትን ማወቅ

«አንድን ሰው ፣ ሰው መሆኑን ለማወቅ ስትፈልግ ኃላፊነት ያለበትን ሥራ ሰጥተህ ሞክረው ያን ጊዜ በሥራው ትመዝነዋለህ ? የሚል የአንድ ብሔር ምሳሌያዊ አነጋገር አለ ። ነገሩ መልካም ነው ምክን ያቱም ሰነፍ ሰው አዋቂዎች በብዙ ድካም የሠሩትን ሁሉ እንደ ከንቱ ነገር ይቆጥረዋል ። ሠራተኛውን መንቀፍ ፣ ማሰናከልና ዓላማውን መቃወት ዓይነተኛ ተግባሩ ነውና ነው ።

ይሁን እንጂ ትንሽም ይሁን ትልቅ ለሁሉም ኃላፊነት ተሰጥቶታል ። ለምሳሌ ገበሬው ለሚያርሳቸው በሬዎችና ለሚያስተዳድራቸው ቤተሰቦች ከዚያም አልፎ በብሔር ደረጃ የእህል ምርት ማቅረብ ይኖርበታል ወዛደሩም ለፋብሪካው ፣ ነጋዴውም ለንግዱ ፣ እረኛውም ለመንጋዎቹ፤ አስተዳዳሪውም ለሠራተኞቹ ጸሐፊውም ለዶሴዎቹ ፤ አስተማሪውም ለተማሪዎቹ ፣ ካህኑ ለቅዳሴው ፣ መዘምሩም ለማኅሌቱ ተላላኪውም ለቁልፉ ኃላፊነት አለባቸው ታዲያ ስንቶች ናቸው ኃላፊነታቸውን የሚገነዘቡት ?

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስረዱን ከዝቅተኛ ደረጃ ተነሥተው ኃላፊነታቸውን በማወቅ የሠሩት ሙሴና ዳዊት ከበግ እረኝነት ተመርጠው የእስራኤል መሪ ለመሆን በቅተዋል እነ አሞጽ ከላም ጠባቂነት ወደ ነቢይነት ተጠርተዋል ። እነ ጴጥሮስ ከዓሣ አጥማጅነት ለሐዋርያዊ አገልግሎት ተፈልገው የክርስቶስን ሕዳሴና ተግባር ለመመስከር ዕድል አግኝተዋል ። ማንኛውም ሰው ትልቅ ኃላፊነት ያለው መሆኑን የሚያሳውቀው በሥራው ነው እዎ ብዙዎች ከትልቅ ደረጃ የደረሱ በሥራ ታታሪነታቸውና ኃላፊነታቸውን ባለመዘንጋታቸው መሆኑን ተረድተናል ።

በዚሁ አንፃር በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር የምንሠራው ሠራተኞችስ ኃላፊነታችን አውቀን የምንሠራው ስንቶቻችን ነን ? ከበትረ ክናው እንስቶ እስከ አፃፄጥኀት (በር ዘጊ) ድረስ ኃላፊነት እንዳለብን እናውቃለን ቢሆንም ብዙዎች ያለሞያቸውና ያለ ዓላማቸው በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ገብተው የሚፈተፍቱ እንዳሉ ግልጽ ነው ። ታዲያ -- ካላሉት አሁንም ገብቶ መፈትፈቱ አይቀርምና የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ዛሬውኑ መብታቸውን ለማሳወቅ መጣጣር አለባቸው እንላለን ።

ሌሎች ሠራተኞች በማኅበር እየተደራጁ ምርት በማዳበር ለአስተዳደር የሚመቻቸውን በማቅረብ መብታቸው ተጠብቆ ይገኛል በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ግን አንድ ዓይነት የአስተዳደር መልክ አይታይም ። ሆኖም ከነዚህም መካከል ኃላፊነታቸውን የሚያውቁ አንዳንድ የመምሪያ ኃላፊዎች መኖራቸውን እንክድም ። ለማስረጃም ያህል በሚያዝያ ወር ፲፱፻፷ ዓ· ም· ተዘጋጅቶ የወጣው የሰበካ ጉባኤ ደንብ ምስክር ነው ።

ተሻሽሎ የወጣው የሰበካ ጉባኤ መመሪያ የካህናትንና የክርስቲያኖችን አንድነት የሚያበሥር ፣ ቤተ ክርስቲያን ራሷን በራሷ ችላ የምትተዳደርበትን ሕግ የሚወስን ፣ ስለሆነ ፣ ምእመናን የሆን ሁሉ ደስ ሊለን ይገባል ። ምክንያቱም የዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን ያለሰበካ ጉባኤና ስብከተ ወንጌል ወደፊት ልትራመድ አትችልምና ነው ። ታዲያ ደንቡ ንባብ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር አስፈጻሚ ክፍል ስለሚያስፈልገው ሁላችንም ኃላፊነት እንዳለብን አውቀን መምሪያውን በሥራ መተርጐምና ማስተርጐም ይኖርብናል ። ምክንያቱም «ሕግ ተሠርቶላቸው ከሕግ ወጥተው የበደሉ ሰዎች ቅጣታቸው ከመጠን በላይ ሲሆን ፣ ሕግ ሳይሠራላቸው ከሕግ ወጥተው የበደሉ ሰዎች ቅጣታቸው በመጠን ነው» ተብሎ ተጽፏልና ፣ ሕግ ወጥቶ ባንፈጽመው የሚያስወቅሰንና የሚያስፈርድብን በእኛ ላይ ስለሆነ ክርስቲያኖች የሆን ሁሉ ኃላፊነቱ የሁላችን መሆኑን አውቀን የሰበካ ጉባኤውን ደንብ በሥራ እንተርጉመው ።



www.ethiopianorthodox.org

# የሰበካ ጉባኤን ለማደራጀት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባዔን ለማደራጀትና ለማጠናከር በቅርብ ጊዜ አዲስ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ አሻሽሎ አውጥቷል ። የወጣው ደንብም ፵፬ ገጽ ያለው መካከለኛ ጥራዝ ሲሆን ስለ እያንዳንዱ የካህናትና የሕዝበ ክርስቲያን የሥራና የሥልጣን ሁኔታ የሚያብራራ ክፍሎች ያሉት ነው ። በዚህ መካከለኛ ጥራዝ በሁለተኛው ገጽ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን ሀ/ ስለ ምርጫና ሹመት ፤ ለ/ ስለ ገንዘብ አስተዋጽኦ፤ሐ/ ስለ ፍትሕ መንፈሳዊ ፤ መ/ስለ ካህናት ማስጠንቀቂያ የሚናገረውን አሳፍሮት ይታያል።

ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደው ሙሉ ቃል ሲሆን ስለ ጠቅላላው የሰበካ ጉባዔ ጉዳይ ማብራሪያ እንዲሰጡን የሰበካ ጉባዔ መመሪያ ኃላፊ የሆኑትን አቶ አበራ በቀለን ጠይቀናቸው የሰጡንን መልስና ጥያቄ እነሆ ።

ጥያቄ ፤ አቶ አበራ በቀለ የሰበካ ጉባዔ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ይህ የሰበካ ጉባዔስ በእንዴት ዓይነት ቦታዎች መቋቋም እንዳለበት ቢገልጹልን ?

መልስ ፤ የሰበካ ጉባዔ ማለት ስሙ እንደሚያመለክተው ሰበካ ክልል ማለት ሲሆን ጉባዔ ደግሞ ማኅበሩን የሚያመለክት ነው የሰበካ ጉባዔ ማለት እንግዲህ ምእመናንና ካህናት ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ዓላማ ተሰብስበው ወኪሎቻቸውን ለመምረጥና ለመመረጥ የሚችሉና ቤተ ክርስቲያንን በሀብትና በአገልግሎት የሚረዱ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች በአንድ ዓላማ ሥር ተሰብስበው የሚገኙበት ጉባዔ ማለት ነው ።

የሰበካ ጉባዔ የሚቋቋምባቸው ቦታዎችም አብያተ ክርስቲያናት ባሉበትና እንደዚሁም የቤተ ክህነት ጽ/ቤት በሚገኝበት ሁሉ እንዲቋቋም አዲስ የወጣው የመንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ ያስረዳል ።


ጥቂያ ፤ የዚህ የሰበካ ጉባዔ መቋቋም ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚሰጠው ጥቅም ምንድነው ? ለሕዝበ ክርስቲያኑስ ምን ዓይነት ጥቅም ያስገኛል ብለው ያስባሉ ?

መልስ ፤ በዚህ የሰበካ ጉባዔ መቋቋም ቤተ ክርስቲያኒቱ በብዙ ነገር ልትጠቀም ትችላለች ፩ኛ/ ካህናቱ አገልጋዮቿ በሚያስፈልጋቸው የዕለት ኑሮ በገንዘብ በኩል ባለው ችግራቸው ሊረዱ የሚችሉበት ዓይነተኛ መንገድ የሰበካ ጉባዔን በማቋቋም ነው ይህም ማለት ትልቅ የገቢ ምንጫቸው ሊሆኑ የሚችሉት እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ምእመናን ስለሆኑ ሁለቱን ሊያስተባብርና ሊያቀራርብ የሚችለው የሰበካ ጉባዔ መቋቋም በመሆኑ በዚህ ረገድ የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች ለመጥቀም ይቻላል ። በዚህም ምክንያት አገልጋዮች በሚገባ ከተቋቋሙ ደግሞ ኑሮአቸውም ሊሻሻል ከተቻለ ቤተ ክርስቲያንም በሚገባ አገልግሎቷ ሊስፋፋ ይችላል ማለት ነው ። ፪ኛ/ ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚሰጠው ጥቅም ስለተባለው ካህናቱ የተሟላ አቋም የተሟላ ትምህርት ካላቸው ምእመናኑን በሚገባ የመንፈሳዊ አገልግሎት ሊያበረክቱ ይችላሉ ። ለምሳሌ መንፈሳዊ አገልግሎት ስንል ማናቸውም የሰበካ ጉባዔ አባል (ምእመን ) የገንዘብ አስተዋጽኦ የከፈለ ሌላውንም መንፈሳዊ ግዴታውን ያሟላ በነፃ ጸሎተ ፍትሐት ይደርስለታል ። እንደዚሁም በነፃ ክርስትና ያስነሳል ሌሎችንም ይህን የመሳሰሉትን መንፈሳዊ አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል ማለት ነው ። ከዚህም በተረፈ እዚያው ለሚገኙት ካህናትም ሆኑ ምእመናን ሰበካ ጉባዔው እስካለ ድረስ በኅብረት እንደመመራቱ መጠን ማናቸውንም ነገር በጋራ ሊቋቋሙት ይችላሉ ጥቅሙ እንግዲህ ከሞላ ጐደል ይህ ነው እላለሁ ።

የሰበካ ጉባዔ መቋቋም ለቤተ ክርስቲያኑና ለካህናቱ ትልቅ የገቢ ምንጭ ይሆናል ብለዋል ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን የሚዋጣውን ገንዘብ በቀጥታ ለካህናት ደመወዝ ብቻ ነው የምታደርገው ማለት ነው ? ወይንስ ሌላ የሚሠራበት ነገር አለ ?

መልስ ፤ የቤተ ክርስቲያን የወደፊት የኤኮኖሚ አቋም የሚንቀሳቀሰው በምእመናን የገንዘብ አስተዋፅኦ ነው ለማለት ይቻላል ። እርግጥ ሌላም ከመንግሥት አነስተኛ ድጐማ ቢኖርም ቅሉ ከፍተኛው እርዳታ ይገኛል ተብሎ የሚታሰበው ከምእመናን ነው ። እስካሁንም ድረስ ቤተ ክርስቲያን በምእመናን ሃብት አልተጠቀመችም የመጠቀሚያው ጊዜ አሁን ነው ። ስፊ የገቢ ምንጭ ይሆናል ተብሎም ይገመታል ። ይህ የገቢ ምንጭ ደግሞ እርግጥ ነው ። ቅድም እንደተባለው ለካህናት መተዳደሪያ ብቻ አይደለም ሌላም ገንዘቡ የሚውልበት ብዙ ነገር አለ ። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ የሚገኙ ብዙ ችግረኞች ይኖራሉ። እነርሱን ለመርዳት ምግባረ ሰናይ ድርጅትን ለማቋቋም አንዳንድ ድኩማንን ከዚህም አልፎ በእርጅና የደከሙ ወይም ደግሞ እጓለ ማውታ እነዚህን ሁሉ ለመርዳት የሚቻልበት መንገድ






በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባዔት ጠቅላላ አቋም ሥዕላዊ መግለጫ ።



www.ethiopianorthodox.org


አለ ። እንደዚሁም ደግሞ ልዩ ልዩ የልማት የትምህርትም ሌሎችንም ማኅበራውያን አገልግሎት ለመስጠት ይቻላል ማለት ነው ። ስለዚህ በዚህ ገንዘብ ብዙ ነገሮችን መሥራት ይቻላል ። ለካህናቱ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለምእመናን ጭምር ለሁሉም አንድ ላይ ለቤተ ክርስቲያንም እድገት የሚረዳ ስለሆነ ይኸውም የገቢ ምንጭ ለጠቅላላው ቤተ ክርስቲያን ለሰበካ ጉባዔም ሆነ ለቤተ ክህነቱ ዓይነተኛ እርዳታ ይሆናል ። ተብሎ የሚጠበቅ ነው ። ልማት ሲባል አብዛኛው ጊዜ ምርትንም የሚመለከት ሊሆን ይችላል ። እርግጥ ቤተ ክርስቲያን አቋሟ ምርትን በማምረት የተመሠረተ ባይሆንም አገልጋዮቿ ምርትን ሊያመርቱ መቻላቸው እሙን ነው ። ቢሆንም ይህ ካህን ነው ያ ምእመን ነው በማለት በምርት ሥራ ላይ ልዩነት መፍጠር አይቻልም አሁን እንደምናየው ብዙዎች ካህናት በምርት ሥራ ላይ የተሠማሩ አሉ ። በትርፍ ጊዜአቸውም ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ አሉ በውጭ ሶሻሊስት አገርም ሆነ በሌላውም ሀገር እንደምናየው በምዕራብ ብዙ ካህናት በምርት ሥራ ላይ እየተሠማሩ ቤተ ክርስቲያንን የሚረዱ አሉ ። በኛም በትንንሹ የምርት ሥራ ላይ እንደ ጉጆ እንዱስትሪ የመሳሰለውን ያቋቋሙ አሉ ። ለወደፊትም ለማቋቋም ያቀዱ አሉ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከተማ እንኳን የዘይት መጭመቂያ አነስተኛ ፋብሪካ እየተዘጋጀ ነው ይህም እንግዲህ ለሰበካው ምእመን ብቻ ሳይሆን እንዲያውም አልፎ አልፎ ተርፎ በዚያ አካባቢ ለሚገኝ የከተማ ሕዝብ ሁሉ ይዳረሳል።ሌላ ደግሞ እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት አኗኗራቸው እንደ ገዳም ስለሆነ በዚያ አካባቢ የሚገኙ መነኮሳት አንድ የከብት እርባታ እንዲቋቋም ማዘጋጀታቸው የታወቀ ነው። በውነቱ ራሴ ሄጄ አይቼዋለሁ የሚያስደስት ነው ። ምእመናኑ ከውጭ ሌላ የቀን ሞያተኛ ሳይቀጥሩ ራሳቸው አጥሩንም ሆነ ሌላውን የሚያስፈልገውን ሁሉ ልክ እንደ አንድ የቀን ሙያተኛ መሥራታቸው የተረጋገጠ ነው። ሄዶ ለማየት የሚፈልግ ሰው በሩ ክፍት ነው ። ሌላ ደግሞ በቅርቡ ከፋ ሀገረ ስብከት በሊሙ አውራጃ አጋሮ ከተማ ሄጄ እንዳየሁት የሰበካ ጉባዔው ከቀበሌ ጋር በመነጋገር ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የሚውል ሰፊ ቦታ ፈልገው የአትክልት ቦታ እያዘጋጁ ናቸው እንዲያውም በዚህ አጋጣሚ የምናገረው በዚሁ ቦታ የሥጋጃ ፋብሪካ ለማቋቋም ገንዘብ በማዋጣት ላይ ናቸው ። እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የሚሠሩትን የልማት ሥራዎች በብዙ ዓይነት ልንተነትናቸው እንችላለን የቤተ ክርስቲያን ሠዓሊዎች ቅርሳ ቅርስ ፤ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ልታበረክተው የምትችለው ምርት ነው ።

ጥያቄ የሰበካ ጉባዔ መቋቋም አዲስ ነገር አይደለም ከተጀመረ ቆይ ቶአል ቃለ አዋዲም ነበረው አሁን ጥቂት ደግሞ የቆየው ቃለ አዋዲ ቀርቶ ሌላ ቃለ አዋዲ ወጥቷል የቆየውና የአሁኑ ቃለ አዋዲ ልዩነት ምንድነው ?

መልስ ፤ ልዩነት አለው አንድነትም አለው ልዩነቱ በቆየው ላይ በአጥቢያ ደረጃ ለተቋቋመው ሰበካ ጉባዔ የበለጠ ገለፃ ያደርጋል ። ከዚያ በላይ ላሉት ግን ሰፊ ድንጋጌዎች አልወጡለትም ነበር።በአሁኑ ግን በአጥቢያ ደረጃም ሆነ ከዚያ በላይ ላሉት በሰፊው ነው የተዘጋጀው ብዛትም አለው የየአንዳንዱንም ተግባርና ሥልጣን ለይቶ አውጥቶአል ። በቅርጽና በይዘቱ ተመሳሳይ ቢሆንም አዲሱ በጣም ሰፊ ነው ለምሳሌ በአጥቢያ ደረጃም ሆነ በሌላውም በቀደመው ላይ በአንድ አጥቢያ ውስጥ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚል የለውም ይህም ስለ ልማት ምግባረ ሰናይ ስለ ወጣቶች የመሳሰሉት ክፍሎች አልተጠቀሱም በአሁኑ ደንብ ግን እያንዳንዱ ክፍል ተጠቅሷል ሥራና ኃላፊነታቸውም ከዚያው በድንጋጌ መልክ ወጥቷል።ሌላው ልዩነት ደግሞ በሰበካ አስተዳደር ጉባዔ ውስጥ ወጣቶች ተሳትፎ አልነበራቸውም በአሁኑ ግን በአስተዳደር ጉባዔ ውስጥ ወጣቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል ።

ሌላው ልዩነት ደግሞ ምናልባት በውስጠ ታዋቂ ይኖር ይሆናል ግን በግልጽ አልተፈጸመም የሴቶች ተሳትፎ እምብዛም አይታይም ነበር ይህንንም ለመጠቆም በአሁኑ ላይ የጾታ ልዩነት ሳይደረግ የሚል ቃል ገብቶ ሁለቱም ወገኖች በእኩልነት እንዲሳተፉ በር ተከፍቷል ። ሌላም ሰፋ ያለ ልዩነት አለው ወደ መንበረ ፓትርያርክ ደረጃ ሲመጣ ልዩ ልዩ አቋሞች ከላይ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ማእከላዊ አስተዳደር ምእመናን የአመራሩ ተካፋይ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው ። የቀድሞው ግን ለአንድ ጊዜ ተሰብስበው የሚለያዩ እንደ ዓመታዊ ስብሰባ ዓይነት እንጂ የአስተዳደር አቋም ኑሮአቸው ተግባርና ሥልጣናቸው ተለይቶ አልተገለጸም ነበር ።





የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አቋም ሥዕላዊ መግለጫ ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህንን የመሳሰሉ ልዩነቶች አሉት ።

ጥያቄ እስካሁን ድረስ በተቋቋሙበት የሰበካ ጉባኤዎች ምን ዓይነት ውጤት ተገኝቷል ፡?

መልስ እስካሁን በተቋቋሙት ላይ አንዳንድ እንቅፋት ተገኝቷል እንደዚሁም መልካም ነገርም ያየ ንበት አለ ። ሁሉቱም አሉ እንቅፋቱ አብዛኛውን ጊዜ ባለማወቅ ይመስለኛል ። በማወቅ የሚያጠፉት ቢኖር ጥቂቶች ናቸው እንቅፋቱም እንዴት እ እንደሚዘለል እየተጠና ነው ። ግን ከውስጣችን እንቅፋት ባለማወቅ ይሠራሉ ብለን የምናስበው ከካህናት ወገን ነው ። ብዙ ጊዜ የሰበካ ጉባኤ ለማቋቋም ለማደራጀት በሚጀምሩበት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የምእመናን ወደዚያ መምጣትና ምዕመናን አንዳንድ ቁጥጥር በሚያደርጉበት ጊዜ የማይወዱ ክፍሎች አሉ ። በተለይ በንብረት ኃላፊነት ያሉት ምዕመናን አንዳንድ ድስፕሊን ለማስከበር የሚወሰዱትን እርምጃ በመጥላትም ከዛው ከአጥቢያው ካህናት መካከል ብዙ ተቃውሞ መጥቷል ። ይህ ሁሉ እንደ እንቅፋት ተቆጥሯል ። እንዲያውም በዚህ የተነሣ በዚህ ያኮረፉ አንዳንድ ካህናት በየንስሐ ልጃቸው ቤት እየገቡ ምእመናን አስተዋጽኦ እንዳይከፍሉ የወርም የዓመትም አስተዋፅኦ እንዳያደርጉ የሚከለክሉ የሰበካ ጉባኤም ለሌላ ዓላማ የመጣ እንጂ እውነተኛ የቤተ ክስርቲያን አቋም ያለመሆኑን በማስረዳት የሚያወናብዱ አሉ ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተደረገ ነገር ነው።የምናገረው በዚያው በሰበካ ጉባኤ አማካይነት ደመወዛቸው የሚጨመርላቸው መሆኑን ካወቁ ጊዜ ጀምሮ ግን ለሰበካ ጉባኤ መቋቋም ዋና ረዳቶችና ሠራተኞች የሆኑ ብዙ ካህናት አሉ።የዚሁም ሪፖርት ደርሶናል ። እንግዲህ እንቅፋቱ በዚሁ እየተወገደ ነው ። በወጣቶችም በዲያቆናትም ፤ በኩል በገበዞችም በልዩ ልዩ አቅጣጫ መጥቷል ። ለሁሉም ጊዜው እየተራዳ ችግሩም ራሱ ወደ ሰበካ ጉባኤ እንዲጠጉ አድርጓቸዋል እንቅፋቱ እየተወገደ ነው ። የእንቅፋቱም ዓይነት ከቦታ ወደቦታ የተለያየ ነው ሆኖም እንደአካባቢው መፍትሔ እየተፈለገለት ነው ።

ጥያቄ ሰበከ ጉባኤን ማቋቋም ከሕዝበ ክርስቲያኑ የሚፈለግበት ምንድ ነው ? ከካህናቱስ በኩል ምንን አሟልተው መገኘት አለባቸው ይላሉ ?

መልስ ከካህናት በኩል የምናሟላው ብዙ ነገር አለ ። ይኸውም በአስቸኳይ የማደራጀቱ ጉዳይ ነው ። ይኸውም ደንቡ ወጥቷል አሁን እንግዲህ የደረስነው ይህንን በቶሎ ማሰራጨት በቶሎ ይህ ደንብ ተጠንቶ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ተደራጅተውም ምእመናንና ካህናት ማለት የገጠሩ ራቅ ያሉት ካህናትም ሆኑ ምእመናን የሚያምኗትን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚያገለግሉበት መንገድ የተተለመው በዚህ በደንቡ ውስጥ በተሰጠው ድንጋጌና መመሪያ ስለሆነ ያንን በመከተል በቶሎ እንዲደራጁ ማድረግ የሚያስፈልግ ስለሆነ በኛም በኩል ሆነ በሐዋርያዊ ድርጅትም በቤተ ክህነት አቋም ያላቸው ድርጅቶች ሁሉ ተባብረው ይህንን ባስቸኳይ ማቋቋሙ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅምና የቤተ ክርስቲያንንም አገልግሎት የተሟላ የሚያደርግ ነው ብየ ነው አስተያየት የምሰጠው ። በዚህ ሥራ ላይ ነው አሁንም የቆምኩት አሁን ያለን በበኩላችን በሰበካ ጉባኤ ፤ በወጣቶች መመሪያ ፤ በሌሎችም መመሪያዎችና ክፍሎች ጋር በመተባበር የምንሠራው ይህንኑ ለማሠራጨትና ወደ ልዩ ልዩ ቦታ ለማዳረስ ነው ። ይኸው እስካሁን አራት ክፍለ ሀገሮችን አዳርሰናል ። አምስተኛ ያው አዲስ አበባ ከተማነው እንደ አንድ ሀገረ ስብከት ተቆጥሮ እንግዲህ ወዲህ ደግሞ ወደሌሎች ክፍላተ አህጉር ለመሄድ ፕላን እያወጣን ነው ምናልባት አሁን ወደ ሰሜን ሳይሆን አይቀርም ጉዞአችን ሥራችንን የጀመርነው በማእከላዊውና ደቡብ ክፍላተ ሀገሮች ነበር አሁን ወደ ሰሜን ነው እንግዲህ እግዚአብሔርን ኃይልና መከታ በማድረግ እንሠራለን እ ግዚአብሔርም እንደሚረዳንና እንደ ማይለየን እምናለሁ ለዚሁም የሁላችን ጸሎት ነው ሲሉ ገለጻቸውን ደምድመዋል ።



# ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ

በእውነት ጽሑፍ የተጻፈውን እነግርሃለሁ ፤ በዚህም ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም ። ዳን፲፣-፳፩ ።

ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ መላእክት ለሰዎች ብዙ አገልግሎትን ሰጥተዋል ። መንፈሱ ተራቁቶ በፍርሃትም ተውጦ የሚንቀጠቀጠውን ከከፉ ነገር በመጠበቅ ብዙዎችን ረድተዋል ።

ሰው ሊፈጽመው ያሰበውን ተንኮል መላእክት ወደ መልካም ነገር ይለውጡታል ። መላእክት የደስታ የምሥራች ፤ ነጋሪዎች የድኩማን ደጋፊዎች የድሀ አደግ ረዳቶች ናቸው ። በተለይም ቅዱስ ሚካኤል በችግራቸው ጊዜ እየተገኘ የረዳቸውና ከብዙ መቅሰፍትም ያዳናቸው እጅግ ብዙዎች ናቸው በብዙ ቅዱሳት መጸሕፍትም ተጽፏል።

በመጽሐፈ ሔኖክ ስለቅዱስ ሚካኤል በጐ አድራጊነትና ረዳትነት እንዲህ ይላል ። ሰው ባደረገው ነገር ለሕዝቡ ታዛዥ ነውና ከከበሩ መላእክት አንዱ ሚካኤል ነው ። ሄኖክ - ፮፣፭

አዎ ቅዱስ ሚካኤል የተጐዱትን የሚረዳ የተቸገሩትን ሕዝቦች ፈጥኖ የሚያፅናና የተጨነቀችውንም መንፈስ በቅጽበት የሚያድን በመሆኑ ለሰዎች ባደረገው በጐነት ሰማያዊ መልአክ ሲሆን ለሰዎች ግን ቅን ጠባቂ ነውና ታዛዥ ተብሏል ።

ስለዚህ ነው በትንቢተ ዳንኤልም ፤ ከዋነኞቹም አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ ተብሎ በችግር ጊዜ ለእርዳታ ምን ያህል ፈጥኖ እንደሚደርስ የተጻፈው ዳን- ፲፣፲፫ ፤

ባጠቃላይ ቅዱስ ሚካኤል ለሰው ልጆች ረዳትና ርኅሩኅ መልአክ በመሆኑ የተጨነቁ ሁሉ ወደእርሱ ልመናቸውን ሲያቀርቡ ከእግዚአብሔር ምሕረትን እየለመነ ከጭንቀታቸው ያሳርፋቸዋል ።

ቅዱስ ሚካኤል በተራዳኢነቱ ከሞቱ ያዳናቸው ከመቅሰፍት የሠወራቸው መርገሙን ወደበረከት የለወጠላቸው ብዙዎች ሲሆኑ ፤ በተለይ ፈጥኖ ደራሹ



ተራዳኢው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል



www.ethiopianorthodox.org

ሚካኤል ሰኔ ፲፪ ቀን ያዳነው ባሕራን የተባለ ወጣት ይገኝበታል ።

ይህም እንዲህ ነው ፤ ከብዙ ዘመናት በፊት በአንድ አገር አንድ ኃብታም ሰው ይኖር ነበር ባጠገቡም የነበረች አንዲት ድሀ ሴት ወንድ ልጅ ወለደችና ይህ ሕፃን አመጸኛውን ሀብታም እንደሚወርስ ንግርት ይሰማ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ሀብታሙ ሕፃኑን በልዩ ልዩ ዘዴ ከእናቱ ወሰደና በባሕር ጣለው ። ግን እግዚአብሔር ይህን ሕፃን በአንድ የበግ እረኛ አማካይነት አዳነው ።

አሁንም አመጸኛው ሀብታም የሞት ደብዳቤ አስይዞ ወደሀገሩ ላከው ። እግዚአብሔርም ሊያድነው ወዶአልና እንደገና እግዚአብሔር በመልእክተኛው በቅዱስ ሚካኤል አማካይነት የሞቱን ደብዳቤ ወደ ሕይወት ለወጠው ። ከዚህም በላይ «ያ » ሕፃን ልጅ የሀብታሙን ሴት ልጅ እንዲያገባና ሀብቱን እንዲወርስ እግዚአብሔር በመልእክተኛው በሚካኤል አዘጋጀ።ሀብታሙ ከሄደበት ቢመለስ ሁለት ጊዜ እንዲሞት የተመኘለትና እንደሞተም የቆጠረው ሕፃን ሀብቱን ወርሶ፤ልጁን አግብቶ ደረሰበዚህ ጊዜ ደንግጦሞተ።የባለጸጋው ሚስት ም በባሏ ሞት ደንግጣ ወዲያው ሞተች ሁለቱም በአንድ ጉድጓድ ገቡ ከዚያ ላይ ነው ቅዱስ ሚካኤል የሰዎች ታዛዥ ሆኖ ምሕረትን ከእግዚአብሔር ይዞ የተገፉትን ሊረዳ ተጋፊዎችን ሊቃወም ይገሠግሳል ተብሎ የተነገረው ።

እግዚአብሔር ሊረዳው የፈለገውን የሰው ሀሳብ ሊያግደው አይችልም እንደተባለው እግዚአብሔር ሊረዳው ያሰበውን ባሕራንን የባለጸጋው ሀሳብ ሊያጠፋው ከቶ አልቻለም ። ጠባቂውና ረዳቱ ተራዳኢው ቅዱስ ሚካኤል ነውና ። «ያ» ባለጸጋ ሀብቱ የተሰጠው የሌላቸውን እንዲረዳበት መሆኑን ባለመገንዘቡ ድሆችን አይረዳበትም ነበር ። እግዚአብሔር ግን ድሆችን ማበልጸግ ፤ ባለጸጎችን ማደህየት የሚችል አምላክ በመሆኑ የድሀዋን ልጅ ሊያበለጽገው በመውደዱ በተራዳኢው መልእክ ቅዱስ ሚካኤል አማካይነት የባለጸጋውን ሀብት ለድሀዋ ልጅ ለባሕራን አወሰረው ።

ይህ ነገር ቀደም ሲል በግልጽ በመላእክት ልሳን ስለተነገረ ነበረ እግዚአብሔርንና ቅዱስ ሚካኤልን ለመገዳደር ሲል አመጸኛው ሀብታም ባህራንን ሊያጠፋው ፈለገው ።

ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሊታደገው የፈለገውን የሰው ሀሳብ ሊጐዳው ስለማይችል ቅዱስ ሚካኤል በተዘዋዋሪ መንገድ የባለጸጋውን ሀብት ከነቤቱ አወረሰው ።

ቅዱስ ሚካኤል በዚህ ጊዜ ነው ለባሀራን ከፍተኛውን እርዳታ ያበረከተለት ። ወደ ባሕር በተጣለ ጊዜ ጉዳት እንዳይደርስበት ጠብቆታል ። የሞቱን ደብዳቤም ወደሕይወት ለውጦታል ።

ወጣቱ የሚመልስበትን መንገድና ሀገር የማያውቀው ስለሆነ ቀናውን መንገድ መርቶታል ።

ስለዚህ ነው መላእክት እንዲህ ዓይነት የግፍ ግፍ በደል ሲደርስ ፈጥነው ስለሚረዱን እኛም በችግራችን ጊዜ የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ፈጥናችሁ አድርሱልን በማለት የምናከብራቸው

ቅዱስ ሚካኤል የተማጸኑትን ከብዙ ችግር ያድናቸዋል ። የታመሙትን ይፈውሳቸዋል የተጨነቁትን ያፅናናል ፤ የተሸበሩትን ያረጋጋል ፤ « ያ» ሕፃን እንዲገደል የተፈረደበት በድኅነቱ ነበረ ። ግን እናቱ በታሪክ እንደሚነገርላት ቀደም ብላም በቅዱስ ሚካኤል ረዳትነት የምታምንና ከችግሯም ሁሉ እንዲረዳት ቅዱስ ሚካኤልንየምትጠራ ስለነበረችና ልጅዋምረዳት እንደሌለው ተገንዝባ ቅዱስ ሚካኤል ረዳት እንዲሆነው አደራ ሰጥታው ስለነበረ አደራ ጠባቂው ቅዱስ ሚካኤል ልጅዋን ከተወረወረበት መቅሰፍት ሁሉ በሕይወት ጠበቀላት እጅግ አስፈሪና ኃይለኛ ከነበረው ባለጸጋ ቁጣ አድኖ የባለጸጋው ንብረት ወራሽ እንዲሆን አደረገላት ያን ጊዜ የነበረው ቅዱስ ሚካኤል ዛሬም ቢሆን የማይለወጥ ስለሆነ አሁንም እርዳታውን አምነው ለሚጠሩት ይደርስላቸዋል ። ልጆቻቸውንም አደራ ከሰጡት በቸርነቱ ከማንኛውም መቅሰፍት ይጠብቃቸዋል ።

የቀደሙት ቅዱስ ሚካኤልን ዕርዳታና አዳኝነት የቀመሱት ቅዱስ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እያሉ የተናገሩትና በቅዱሳት መጻሕፍት የጻፉትም ፈጣኑ ቅዱስ ሚካኤል ፈጥኖ ስለደረሰላቸውና ከችግራቸውም ሁሉ ስለአዳናቸው ነው ።

ዛሬም እኛ ተራዳኢነቱን አምነን እንጥራው ከችግራችንም ሁሉ ሊያድነን የታመነ መልአክ ነው ። ከችግራችንም ሲረዳን ያን ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ሊያድነኝ መጣ ከቅዱስ ሚካኤል በቀር የሚያፅናናኝ የለም እያልን ልንመሰክር እንችላለን ።

የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ። ያድናቸውማል ተብሎ ተጽፎአልና መዝ- ፴፫፡፯

ተስፋ ጥሩነህ



# ሃይማኖት በሶሻሊስት አገሮች

አንዳንድ ሰዎች ሃይማኖት በሶሻሊስት አገሮች እንደሌለ አድርገው በማቅረብ ለማሳመን ይጥራሉ ። ግን ይህ ስህተት ነው በተለይም የሶሻሊዝም በኩር ከሆነችው ከሶቪየት ኅብረት ጀምሮ በምሥራቅ አውሮጳ በሚገኙ የሶሻሊስት አገሮች ሁሉ ዘንድ አብያተ ክርስቲያናት የጥንት አቋማቸውን ይዘው በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ይገኛሉ ። ምዕመናንም ወንጌልን በመቀበል ሆነ ፤ ተቀብለው በማስፋፋት ተግባር በመተባበር «በነፃ የተቀበላችሁትን በነፃ ስጡ» ብሎ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን ትእዛዝ በመከተል ይሠራሉ በገንዘብም ረገድ ወደ ኋላ ሳይሉ ሠርተው ያገኙትን መብአ ከመቸር አላፈገፈጉም ።

ቤተ ክርስቲያን ትምህርትዋና ምዕመናንዋ በሶሻሊስት አገሮች የሚገባ አቋማቸውን ይዘው በኅብረተሰባዊነት መርሆ መሠረት ከማንኛውም ዜጋ



ኒኮላይ ዘቦሎትስኪይ የዓ. አ. ክርስቲያናት ማኅበር በክፍል 2 የፍትሕና ያገልግሎት ጸሐፊ ሲሆኑ ቀደም ሲል በሊንንግራድ መንፈሳዊ አካዳሚ የቤ. ክር. ታሪክ መምህር ነበሩ ፤

ጐን ተሰልፈው ግዴታቸውን በመፈጸም ላይ መሆናቸውን ፤ ብሌኒንግራድ የቲኦሎጊ አካዳሚ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከፍተኛ መምህር (ፕሮፌሰር) የነበሩትና አሁን ግን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ፍትሕንና አገልግሎትን የሚመለከተው ክፍል የጥናት ጸሐፊ የሆኑት ፕሮፌሰር ኒኮላይ ዛቦሎትስኪ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተጠባባቂነት እየተዘጋጀለሚወጣው ወርኃዊ መጽሔት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡትን መልስ ቀጥለን አቅርበነዋል ።

ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ በሶቪዬት ኅብረት ውስጥ ስላለው የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ቢያብራሩልን ?

መልስ መልካም ነው ። ባጠቃላይ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት ወይም በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለው አስተያየት እየተለወጠ እስከዚህ ደርሷል ። ስለሆነም ዛሬ በየመንገዱና በየአደባባዩ ካህናት ቢያጋጥሙን በይፋ ልናነጋግራቸው እንችላለን ።

በዚህም ማንም ሰው አይገረምበትም እንግዲህ በዚህ አንፃር ሲታይ ስሜቱ ወይም አስተያየቱ እየተለወጠ መምጣቱን ያሳየናል ። ሁኖም ሁኔታው ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው ሊለያይ ይችል ይሆናል ።

ጥያቄ በጽሑፍዎ ላይ በኅብረተሰብ አገነባብ ወይም ሂደት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ሚና ምን መሆን እንዳለበት ጠቅሰዋል ። ምንን ሲያስረዱ ነው ?

መልስ በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን ሕዝባዊት ናት ስለሆነም ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያደርጉት ስብከታቸው አማካይነት ሰዎች መልካም ዜጎች እንዲሆኑ ሲያሳስቡም ሆነ ቤተ ክርስቲያን በማኅበራዊ ኑሮ ረገድ የሚገባትን ስትሠራና ያለባትን ግዴታ ስታሳይ ይህ እንግዲህ ተጠቃሎ ወደ ኅብረተሰብ አገነባብ ይተረጐማል ማለት ነው።



ጥያቄ ስለኅብረተሰባዊ የክርስቲያን ግንዛቤ ጠቅሰው ነበር ስለዚህ ቢያስረዱ ?

መልስ የሶሻሊስት አቋሞች ከክርስትና አቋሞች ጋር እጅግ በጣም ስለሚቀራረቡ ፤ ይህ አገላለጽ ትርጉም ያገኛል ። ለእኔ የክርስትና እምነቴና የሶሻሊስት አቋም ወይም ሕግጋቱ ተለያይተው አይሄዱም ። ለምሳሌም ያህል ፍቅር ወንድማማችነትና መልካም ምግባር በነዚህ ሁለት አቋሞች ውስጥ ተባብረው ይገኛሉ ይሁን እንጂ በሃይማኖት ላይ የተቃውሞ ፕሮፓጋንዳ ይካሄድባቸው በነበረባቸው ዓመታት ይህ አስቸጋሪ ነበር ። ስለሆነም ልዩነት ቢኖር ሳያጋንኑ ለማስተባበር ይቻላል ።

ጥያቄ ከአብዮቱ በፊት በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል መግባባት አልነበረም እንደማስታውሰው በሁለቱ አቋሞች መሀል መግባባት እንደሌለ አድርገው ተችተው ነበር በዚሁ ትችትዎ ውስጥ ከአብዮቱ በፊት ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት አንዱ አካል እንደሆነችና በገገርዎቹ እጅ እንደነበረች አመልክተዋል ። ይህ እንዴት ነው ?

መልስ ከአብዮቱ ብፊት የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እርስ በርሱ በሚቃረን ደረጃ ላይ ነበር ። እንዲህም ስል ቤተ ክርስቲያን ትከበር ነበር ፤ ጳጳሳትም ከፍተኛ ሥፍራ ነበራቸው ብዙ የመነኰሳትም ደብሮች ነበሩ ። ይሁን

www.ethiopianorthodox.org

እንጂ ከእውነት አንፃር ብንነጋገር ቤተ ክርስቲያን ድሃ ነበረች ከዚህም በስተቀር የመንግሥት ባሪያ ሁና ከጴጥሮስ ታላቁ ዘመን ጀምራ ቀይታለች ጳጳሳቱ የሌላቸው ቢሆንም ቅሉ ካህናቱና ምዕመናኑ እጅግ በከፋ ሁኔታ ላይ ነበሩ ስለሆነም ካህናት ድሆችና ያልተማሩ (መሃይምናን) ነበሩ። በአንዳንድ ሥፍራዎች በሥልጣን ላይ ከነበሩ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችም ሁኔታዎች ከዚህ አይሻልም ነበር ። በዚሁ ጐን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በሚገኙ ምሁራን ዘንድ ሃይማኖት ተቀባይነት ነበረው አብዮቱ በመጣ ጊዜ ግን ከአብዮቱ መሪዎች ጥቂቶቹ የሃይማኖት ትምህርት የተማሩ ነበሩ ማለትም በሰሚናሪዮም ነበሩ ታዲያ አብዮቱ ገፍቶ ሲመጣ ቤተ ክርስቲያን ጥገኝነትዋ በመንግሥት ላይ ስለነበር ብዙ አባላትን ከማጣትም በላይ ተጳከመች ።

ጥያቄ እዚያስ በተከታዩ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን በችግር ላይ ነበረች ?

መልስ አለመግባባትና መቃረን ነበር ሁኖም ቅን አስተሳሰብ የተገኘበት ሁኔታ ብቅ አለ ። በኃዘንና በጭንቀት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በተፋጠነ ሁኔታ ንቃትን ታሳያለች ዳሩ ግን መልካምና አመች ሁኔታ ሲያጋጥማት ደግሞ ቅጡ ይጠፋታል ።

ጥያቄ ይሁንና ቤተ ክርስቲያን ያጋጠማትን ቅራኔ በምን ዓይነት ልትወጣው ቻለች ?

መልስ በቤተ ክርስቲያን በኩል ለኅብረተ ሰቡ የወዳጅነት መንፈስ ለማሳየት ሞከርን ። ምንም እንኳን የአስተሳሰብ ልዩነት ቢኖርም ቅሉ በበጐ አድራጐቱ ተግባር ተሰማራን ስለሆነም የመግባባት መንፈስ ተጀመረ ። በተለይም ይህ የሆነበት በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በጀግንነት ጉዳዮች ሁሉ ላይ ተካፋይ ከሆነችበት ጊዜ ይዞ ነው ። ከዚያም ከጦርነቱ በኋላ የቲኦሎጊ ት/ቤቶቻችንን መልሰን አቋቋምን ሌሎችንም ትምህርታዊ ተቋሞች አጠናከረን በአጠቃላይ እ-አ-አ- ከ፲፱፻፵፭ —፵፮ በተማሪዎቻችንና በአዲሶቹ ምዕመናን አማካይነት ክርስቲያኖች መልካምና ታማኝ ዜጐች ሊሆኑ መቻላቸውን አስመሰከርን ።

ጥያቄ የአገርዎ አዲሱ ሕገ መንግሥት የአገሪቱ ዜጐች ሃይማኖት ሊኖራቸው ሃይማኖታቸውን ሊሰብኩ ወይም ሊያስተምሩ ይችላሉ ከማለቱም ሌላ ባንፃሩ ያለማመንም መብት አለው ይላል ይህ ሕገ መንግሥት አዲስ የሶቪየት አስተሳሰብ እንዳለ ያመለክታል ?

መልስ አዎን ይህን ማለት የሚያምንም የማያምንም እኩል መብት አላቸው ማለት ነው ። ስለዚህ ቤተክርስቲያናችን ወይም የማያምነው ክፍል አንዱ በሌላው ላይ ተፅእኖ አያደርግም እርግጥ ሃይማኖት ስላለመኖሩ ፕሮፓጋንዳ አለ ። ሆኖም በሁለታችን መሀል ጥላቻና ቅዋሜን የማያነሣ ፕሮፓጋንዳ የተከተለ ነው የሕገ መንግሥቱ ፶፪ኛው አንቀጽ ይህን በግልጽ ያሳያል፤

ጥያቄ በአነጋገርዎ በአማኞችና በማያምኑት መሀል ልዩነት ባለው ሁኔታ ተናግረዋል ይህ እንዴት ነው ?

መልስ አዎን ልዩነት አለ ይህን ለመገንዘብ በመንፈሳዊ ባሕላችን ውስጥ አምልኮተ እግዚአብሔር ምን ሥፍራ እንዳለው መገንዘብ አለብህ ። ማለትም ዝም ብሎ መጸለይ ሳይሆን በመንፈሳዊ ኑሮ መኖር ጭምር ነው ። እንግዲህ ይህን የመሰለው አምልኮተ እግዚአብሔር በመታወሱ ነው በሕገ መንግሥቱ ውስጥ እንደሌላው ሁሉ መብታዊ ቦታ የተሰጠው ።

በተለይ እንደቤተክርስቲያን ላለች አንድ ንኡስ ክፍል በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ሥፍራ መስጠቱ የመንግሥታችን ታላቅ ግምት የሚያሳይ ነው ።

ጥያቄ ስለመንፈሳዊ ትምህርት እንዴት ነው ? አዲሱ ሕገ መንግሥት ይቀበለዋል ?

መልስ አዎን ሕፃናት ከወላጆቻቸው ዘንድ ይማራሉ ይህም በጣም ጠቃሚ ነው ። ይህንኑ በመጥቀስ አንዱ ሚኒስትራችን የሆኑት ሚስተር ቪ ክሮደቭ በቅርቡ ኢዝቬስቲያ በተባለው ጋዜጣ ሲጽፍ ልጆች በቤታቸው በወላጆቻቸው ዘንድ የሃይማኖት ትምህርት ሊያገኙ መቻላቸውን ጠቅሰው ጽፈዋል እንደዚሁም ለአዋቂዎቹ (ላደጉ ሰዎች) የሚሆን የሃይማኖት ማስተማሪያ ተቋሞች አሉን ።

ሲሉ ፕሮፌሰር ኒኮላይ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል ።

በአገራችን እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ/ ም/ ድረስ የፊውዶ ቡርዣው የገዢ መደብ እስከተገረሰሰበት ድረስ ቤተ ክርስቲያን ያለውዴታዋ በዚሁ አድኃሪ መደብ ሥር ወድቃ ነበር ። አድኃሪውም የገዥ መደብ የቤተ ክርስቲያንን ባለሥልጣኖች በማቀፍ ለካህናቱና ለምዕመናን ግን ምንም ግምት ሳይሰጥ ብዝበዛውን እንዲቀጥል ነበር ከዚህም በስተቀር ቤተ ክርስቲያን የነበርዋት ታሪካዊ ቅርሶች እንዲመዘበሩ ከማድረጉም በላይ የፈረሱት የአብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎች ሳይጠገኑ ቀርተዋል ።

ዳሩ ግን የጭቁኑ ሕዝብ አብዮት ገፍቶ ከመጣ ወዲህ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ባወጣው ውሳኔ መሠረት የማንም ሃይማኖት ከሌላው በላይ አለመሆኑን ፴፩ኛ ዓመት ዓዋጅ ቁጥር ፲፯/፷፯ አስገንዝቧል ስለነሆነም በቤተ ክርስቲያን መብት መሠረት አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማዳረስም ሆነ የማስተማር መብትዋ የተጠበቀ ነው ።



## « ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም »

በዚህ ዓለም ያለ አስገኝ የተገኘ ፤ ያለ ወላጅ የተወለደ ፍጡር አይገኝም በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሥነ ፍጥረት ምንጮች የሆኑትን ባህርያት አስገኝቷል ። እነዚህም ፍጥረታት ተፈጥሮ በሰጣቸው ጸጋ ሲዋለዱ ሲበዙ ተመልሰውም እንዳልነበሩ ሲሆኑ ይኖራሉ ።

ከምድራውያን ፍጥረታት መካከል ከፍተኛውን ደረጃ ይዘው የሚራመዱት የሰው ወገኖች ናቸው ሰዎች የመወለድና የመራባት ከዚያም በኋላ የመሞት ግዴታ ቢኖርባቸውም ክፉውንና በጐውን ለይተው የሚያውቁበት አእምሮ ጠባይ ስለተሰጣቸው በሥጋዊ ሞት ብቻ እንደ ተጠቃለሉ ሕይወታቸው አይከትምም እንደሥራቸው መጠን ዋጋቸውን ወደሚያገኙበት ዓለመ ነፍስ እንደሚተላለፉ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ።

ግን በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከስህተት ላይ እንዳይወድቁ ሊመሩባቸው የሚገቡ ሕግጋት ተጽፈውላቸዋል ። ለሰዎች መመሪያዎች እንዲሆኑ ከተጻፉትም ሕግጋት አንዱ የሰው ልጆች የተፈጥሮ ወገኖቻቸው የሆኑትን ሁሉ እንደራሳቸው አድርገው መውደድ እንዳለባቸው ይጠቁማሉ ፤ ይሁን እንጂ ጊዜ የማይሽረው ዘመን የማይለውጠው ደመነፍስ ባላቸው ፍጥረታት ሁሉ ጸንቶ የሚኖረው የወላጆችና የልጆች ፍቅር ብቻ ሆኖ ይገኛል ፤ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን ፍቅር ለማንም አያደርጉትም አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ከመውደዳቸው የተነሣ ሕይወታቸውን ስለልጆቻቸው አሳልፈው ከመስጠት ወደ ኋላ አይሉም ።

ይህም ሲባል የወላጆችና የልጆች ፍቅር በሰው ወገን ብቻ የተወሰነ አይደለም እንስሳት፤አራዊት፤ አዕዋፍና የመሳሰሉትም ቢሆኑ ልጆቻቸውን ከራሳቸው አብልጠው የመውደድ ጠባይ እንዳላቸው አይጠረጠርም ከፍቅራቸውም የተነሣ እነርሱ ተርበው ልጆቻቸው ቢጠግቡ እነርሱ ሞተው ልጆቻቸው ቢድኑ ስለሚወዱ አደገኛ ጠላት ሲመጣባቸው ለልጆቻቸው አልፈው ይጋረዳሉ ፤ የልጆችና የወላጆች ፍቅር ከደም ከሥጋና ከአጥንት ጋር የተዋሃደ በመሆን ሊመረመር በማይቻል የተፈጥሮ ምሥጢር የተደበቀ ነው ብሎ በአንክሮ ከማለፍ በስተቀር ሌላ ማስረጃ ለማቅረብ አይቻልም ።

በተለይ የሰው ልጆች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸው ፍቅር እጅግ በጣም የጠነከረ ቢሆንም ሳይነጣጠሉ የመኖር ዕድል የሚገጥማቸው በቁጥር ያነሡ ናቸው በግድም ሆነ በውድ ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር ይለያሉ ከሚለዩባቸውም ምክንያቶች ሞት ችግርና በሽተና የመሳሰሉትም ናቸው በተጠቀሱትና በመሳሰሉትም ምክንያቶች ከወላጆቻቸው የተለዩ ልጆች የፈለጉትን በልተውና ጠጥተው የፈለጉትን ለብሰው ለማደግ አይችሉም ። ረኃብ ፤ ጥም ፤ እርዛት ይደርስባቸዋል ። ጤናቸው በሚገባ አይጠበቅም ፤ የትምህርት እጦት የጤና ጉድለት ስለሚደርስባቸው ኃዘን ብስጭት ፍርሃት ድንጋጤ ወዘተ- የመሳሰሉት በቀላሉ ድል ይነሷቸዋል፤ሞራላቸውም እጅግ በጣም ዝቅ ያለ ይሆናል ። ያለ ወላጅ እንክብካቤ ያደጉ ልጆች ኃዘንና ብስጭት ስለማይለዩዋቸው ከሕፃንነታቸው ጀምረው ሸክም ሆነው ከመኖራቸው በስተቀር እስከሚሞቱበት ቀን ድረስ ለሕብረተሰቡ ለሀገራቸውና ለወገናቸው የሚያበረክቱት አገልግሎት ለራሳቸውም የሚያገኙት ጥቅም አነስተኛ ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወላጆች አልባ የቀሩ ልጆች ከፍተኛ ጉዳት እንደሚደርስባቸው የሚያውቅ በመሆኑ ወደ ሰማይ ለማረግ በተቃረበ ጊዜ «ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች አልተዋችሁም » በማለት ለደቀ መዛሙርቱ አብሥሯቸዋል ። ዮሐ-፲፬ ፲፰ ።

ደቀ መዛሙርቱም ከኢየሱስ የተነገራቸውን ቃል አምነው ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ በ፲ኛው ቀን ድንገት እንደሚነጠቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣና ተቀምጠውበት የነበረውን ቤት ሁሉ ሞላው እንሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ መንፈስ ቅዱስ መላባቸው መንፈስ ቅዱስን ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር የሐ-ሥራ ፪-፲፬

ሐዋርያት ከኢየሱስ እርገት እስከ መንፈስ ቅዱስ መውረድ ድረስ አልተለያዩም አልተነጣጠሉም ከቦታ ወደ ቦታም አልተዘዋወሩም በተሰጣቸው የተስፋ ቃል መሠረት ሲጠባበቁ ሰንብተው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው በዚህም ጊዜ ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች ይፈሩ ይደነግጡ ይባቡም የነበሩ ወደ ድፍረት በአእምሮ ጐለመሱ በመንፈስ ታደሱ አንዲት የዕብራይስጥ ቋንቋ ብቻ ያውቁ የነበሩ የተለያዩ ቋንቋዎች ተገለጸላቸውና በማንኛውም ቋንቋ ማስተማር ጀመሩ ።

ከዚያ በኋላ ይህንን ዓለም ዕጣ በዕጣ ተካፍለው ወንጌልን ለማስተማር ተሰማሩ በሚያስተምሩበትም ጊዜ ብዙ ችግር አጋጥሟቸው ነበር ። ችግር ቢገጥማቸውም መፍትሔ ለመስጠት አልተሳናቸውም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ አብሬያችሁ እኖራለሁ ያለው አምላክ አብሯቸው ይሠራልና ማር-፲፮-፳

መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው አሁንም ቢሆን የጠነከረ ኃይል አለው ያቀደውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ይችላል

ተከታዩ በ፲፭ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ሐቀኛ ሰው ይፈለጋል

ሰው ሲባል በሥራ ሒደት በኩል ሁለት ገጽ ያለው ሁኖ ይታያል አንደኛው ይፈለጋል የተባለው ሰው የራሱን ጥቅም በመናቅ የአገሩንና የወገኑን እድገቱንም ሆነ ጥቅሙን የሚወድ ሀብቱን ብቻ ሳይሆን ሕይወቱንም ጭምር ቤዛ አድርጎ አሳልፎ የሚሰጥ በመሆኑ በየጊዜው ለሚነሳው ትውልድ የሚያስመሰግን የሥራ ቅርስ ትቶ ስለሚያልፍ ሥራው ብቻ ሳይሆን ስሙም ከመቃብር በላይ ይውላል ።

ስለእንዲህ ያለው ሰው አንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ሲናገር «ሠርቶ የሚያሠራ ሰው ራሱን በመጥላት፤ ሌላውን በመውደድ ፤ ገንዘቡንም ፤ ሕይወቱንም ለሀገሩ መስዋዕት አድርጎ በማቅረብ የምግባርና የእምነት መልእክተኛ ሆኖ ሁሉን ለማገልገልና ለመርዳት ሠርቶ ለማሠራት ወደ ሥራ ዓለም እራሱ ይሰማራል ሌላውንም ያሰማራል ፤ ካለ በኋላ አስተያየቱን በመቀጠል እንዲህ ያለው ሰው በዚህ ብቻ ሳይወሰን በሕዝቡ መካከል እየተገኘ የተጣሉትን በማስታረቅ ያልተማሩትን በማስተማር የሰላም ሐዋርያ ሆኖ ኅብረተሰቡን አቅሙ በፈቀደለት መጠን ያገለግላል ሰው ይኳችኋል ይህ ነው» ብሎአል ።

እርግጥም ሥራ ራሱ ምስክር ሁኖ ስለሚመሰክር የሰው ምስክር አያሻውም ሲባል ከእውነት ፈቀቅ አይልም። ለምሳሌ ሽቱ በአገልግሎቱ የታወቀ ነው ከዚህም የተነሳ መዓዛው ከእራቱ ማዕዘን በኩል በነፋስ ኃይል እየሄደ ያውዳል በጠረኑ የሰውን ልብ ሲያስደስት ሲያስጎመጅ አድናቆትንም ሲያበረክት ከመታየቱም በቀር በሰው ዘንድ ኃይሉ ሳይበርድ ስሜቱ ሳይቀዘቅዝ ተወዳጅነት ይዞ መኖሩ ለማንም ግልጽ ነው ።

ሠርቶ የሚያሠራ ሰውም ለሠራተኞችም ሆነ ለመልካም ሥራ የጥሩ ሽቱ ተመሳሳይ ስለሆነ በሥራ መዓዛ ሰዎችን ወደ ሥራ ዓለም ይስባል ሥራውም በእራቱ መዓዘን እያወደ ሠራተኞች ሁሉ ሥራን እንዲወዱ ያደርጋል።

ሁለተኛው ደግሞ የማይፈለግ ሰነፍ ሰው ራሱን በመውደድ ለማኅበራዊ ኑሮ ሳይሆን ለግል ጥቅሙ ብቻ እየተስገበገበ አገሩን ወገኑን የሚጠቅምበትን ራሱ በሰው ዘንድ የሚመሰገንበትን አንዳች ሥራ ሳይሠራ ይኖራል። እንዲህ ያለውም ሰው እንደ እቡት ትል ጥቅምን ሁሉ ለራሱ ሰብስቦ ወንድሙ የሱ ሊማኝ የሱ አሽከር በመሆን እጁን እየዘረጋ እሱን ሲለምን እንዲኖር የሚፈልግ በመሆኑ ለኅብረተሰቡ ታላቅ በሽታ ነው ። እንዲህ ያለውንም ሰው ኅብረተሰቡ አይፈልገውም ።

ዲዮጋን የተባለው የግሪክ ፈላስፋ እኩለ ቀን ሲሆን ፀሐይ ብርሃኗን በኃይል በምትሰጥበት ጊዜ የሰው ብዛት በሚገኝበት በአቴና ከተማና በየገቢያው መብራት እያበራ ይዞ ጀመር የተመለከቱትም ሰዎች ሁኔታው ስላስገረማቸው «በቀን ለምን ታበራለህ?» ብለው ቢጠይቁት ሰው እየፈለኩ ነው አላቸው ። ይህ የምታየው ሁሉ ሰው አይደለምን ? አሉት እሱም ይህ ሁሉ ለሀገር ለወገን የማይጠቅም እውነትንም ፤ ሰላምንም የሚፈልግ አይደለም ስለራሱ ጥቅም ብቻ የሚስገበገብ ሐቀኝነትን ፤ ጨዋነትን ትቶ ሌላውን የሚበዘብዝ ፤ ባጭበርባሪነት፤ በእታላይነት የሚኖርና በሐሰት እየማለ የሰውን ገንዘብ የሚነጥቅ ፤ ፍርድ አጉዳይ ፤ በውሸት መስካሪ ፤ ስለሆነ እንዲህ ያለው ሰው አይፈለግም እኔም ሆንኩ አገሪትዋ በመብራት የምንፈልገው እውነተኛ ሰው ነው» ብሏል።

መዝሙረኛው ዳዊትም ይህን አስተያየት በመደገፍ ፤ አቤቱ በድንኳንህ ማን ያድራል ? በማለት ፈጣሪውን በጸሎት ከጠየቀ በኋላ እራሱ ጥያቄውን ሲመልስ በቅንነት የሚሄድ ጽድቅንም የሚያደርግ ፤ በልቡም እውነትን የሚናገር ፤ በአንደበቱም ሰውን የማይሸነግል ፤ በባልንጀራውም ክፋትን የማያደርግ እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር ምሎ ባልንጀራውን የማይከድ እንዲህ የሚያደርግ ለዘላለም አይታወክም ብሎአል መዝሙር ፲፬ ከቁ. ፩—፭

እርግጥም ዲዮጋንም ሆነ ዳዊት እንደተናገሩት ቀን በመብራት የሚፈለገው እንዲህ ያለው ሰው ነው ። ለምሳሌ እንደ አዝማሪ የመሰንቆውን ወይም የክራሩን ቅኝት እየለዋወጠ ልዩ ልዩ ዓይነት ዜማ በመዘመር አድማጮችን በአንድነት እንደሚያስደስት ሁሉ መልካም አሠሪም ሥራንና ሠራተኛውን በአንድነት እንዲተባበሩካደረገ ምርት ይበዛል አገር ወደ ዕድገት ደረጃ ይደርሳል በዚህ መንገድ ኅብረተሰቡ ይበለጽጋል እኩልነት ፤ ተባብሮ መሥራት ፤ ሰላምና ፍትሕ በተግባር ይተረጎማሉ ማለት ነው ።

ሰንባንቱ ፋዘር ቴምፕል እንደጻፈው «ኑሮ የጋራ ነው መኖርም ደስታውንም ችግሩንም አብሮ ለመካፈል ነው በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የግል የሆነ ነገር የለም አንዱን የሚመለከተው ሌላውንም ይመለከታል የጥቂቶች ኃይል የሁሉም ኃይል ነው የጥቂቶችም ድካም የሁሉም ድካም ነው ከሠራተኞችና ከታታሪዎች ጋር በኖርን ቁጥር ሠራተኞችና ታታሪዎች እንሆናለን የነርሱ ኃይል እኛንም ያነሳናል ከሰነፎችና ከደካሞች ጋር ብንኖርም የነርሱ ስንፍና ይጋባብንና እኛን ወደታች ይጎትተናል» ብሏል ።

እርግጥም በኅብረት መሥራትና ከሠራተኞች ጋር እየሠሩ መኖር የሕይወት ዋስትና ሲሆን ከሰነፎች ጋር መኖር ደግሞ ሥራን ወደ ኋላ ስለሚጎትት ሕይወት የተለየው በድን ነው።

ይህንንም እውነት ሊያደርገው የሚችለው በየጊዜው የሚነሱት የሥራ ሰዎችና የመንፈስም ሆነ የጥበብ ምሁራን ሌት ከቀን ያለ ዕረፍት በሥራ የሚናወዙትና ሕይወታቸውንም በሙሉ ለኅብረተሰቡ በድካምና በልፋት የሚያሳልፉት ሥራ የተባለው ቃል በምርት እንዲተረጎም ታሪክም የክብር ቦታውን ይዞ እንዲገኝ በማለት ነው ። ይህም በቃል ብቻ ተውጦበት ግባር ሳይገለጽ ከቀረ ግን ሥራ ያለ ትርጉም ስለሚቀር የታሪክም ሆነ የሥራ ብርሃን ለሚሠራላት ትውልድ ጨለማ እንጂ ብሩህ ሊሆን አይችልም ስለዚህ በዕውቀት እየተደራጀ ፤ እራሱን የሚችልና ሌላውንም የሚያስችል አገሩንም እንድትበለጽግ ሌት ከቀን የሚጥር ፤ ስለ ሀገሩና ስለ ሕዝቡ ኑሮ የሚታገል ፤ ለወገኑ ሀብትን ለማበርከትና ትውልድንም የዕውቀት ከበርቴ ለማድረግ የሚጣጣር አገራችንም ቤተ ክርስቲያንም እንደ ዲዮጋን በመብራት ሰው የሚፈልጉበት ጊዜው አሁን ነው ።

ወጥ የሚጣፍጠው በድስቱ ትልቅነት ሳይሆን ከአሠራሩ ነው ሥራም ጣፋጭ የሚሆነው በትምህርት ብዛት ሳይሆን ዕውቀት በሥራ የተገለጸ እንደሆነ ነው በዚህ አኳኋን የሕክምና ባለሙያ የሆነ ሁሉ ያገኘውን እውቀት በሥራ እየገለጸ ሕዝቡን በማከም በሽታ ጠፍቶና ሁሉም ጤነኛ ሆኖ ወደ ሥራ ከተሰማራ ጤነኛ ዜጋ ነወና ይፈለጋል ።

አስተማሪም ድንቁርና እንዲጠፋ ዕውቀት እንዲስፋፋ ካደረገ ጥሩ ሰው ነውና ይፈለጋል ዳኛም ቀጠሮ ሳያበዛ በእውነት ስለ እውነት ከፈረደ መልካም አገልጋይ በመሆኑ ይፈለጋል ነጋዴም ተመኑን ጠብቆ የተፈቀደለትን ትርፍ እያገኘ ደንበኞቹን በሚገባ ካስደሰተ ታማኝ ሰው ነው ይፈለጋል ።

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ተባብረው ሲሠሩ ነው ኅብረተሰብ ሊበለጽግ የሚችለው ሰዎች የተፈጠሩት እርስ በርስ እንዲረዳዱ ፤ የኑሮ ቀንበርን አብረው እንዲሸከሙ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

---

# «ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች.»

ከ፲፫ኛው ገጽ የዞረ

ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የምትመራ ስለሆነች «ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም » የሚለውን አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ ወላጆች የሌላቸው ን ልጆችና ረዳት ዘመድ ያጡትን ባልቴቶችና ሽማግሌዎች ታፅናናለች ።

በአሁኑ ጊዜ በሃገራችን በየቦታው ወድቀው የሚታዩት ወላጅ የሌላቸው ሕፃናት ነበሩ ቢሆንም መንግሥት ወላጅ ያጡ ሕፃናትን በመሰብሰብ ላይ ይገኛል ። በተለይ ኅብረተሰቡን እኩል አድርጎ በመመልከት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ያለወላጆች የሚገኙትን ልጆች በቸልታ ሊያልፋቸው አልፈለገም « ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች አልተዋችሁም» የሚለውን ቃል )መፈጸር ይዞ በመነሣት ፤ ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም/ ወላጆች የሌሏቸውን ፩ሺህ ፱፻ ልጆች ሰብስቦ ወደ ወዳጅ ሀገር ለነፃ ትምህርት ሲልክ በዚህ መንገድ ሌሎችንም ልጆች የመርዳት ዓላማ እንዳለው ጭምር ተናግሯል ። የተቀደሰ ዓላማ በመሆኑ ቤተክርስቲያንም ሆነች ሌሎች በጎ አድራጊዎች ሊተባበሩበት የሚገባ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች እንደማይተዋቸው ከመናገሩም ሌላ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ የሥራቸው ተባባሪ በመሆን እንደሚረዳቸው ገልጾላቸዋል ። ለደቀ መዛሙርቱ የተነገረው ቃል በእነርሱ ዘመን ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም የእነርሱን ዓላማ ተከትለን ለምንሠራ ለእኛና ከእኛ ቀጥለው ለሚነሱ ሁሉ የሚተላለፍ ነው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የማጽናናት የድፍረት የተሐድሶ መንፈስን እንደላከላቸው ለእኛም እንደሚልክልን አንጠራጠርም የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ለመሆን እንድንበቃ፣ ፍቅርን ፣ ሃይማኖትን ተስፋን ገንዘብ አድርገን አንድነታችንን አጠንክረን ሳንለያይና ሳንነጣጠል የዕለት ተግባራችን ማከናወን አለብን ከዚህም ጋር ወላጆች የሌሏቸውን ልጆች መርዳት የተፈጥሮ ግዴታችን ነው ትዕዛዙን አክብረን ሕጉን ጠብቀን ከኖርን እግዚአብሔር አምላካችን ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች አይተውንም ለእኛ ከኃዘናችን የሚያጽናናን መንፈሳችን የሚያድስ የድፍረት ና የተሐድሶ መንፈስን ይልክልናል ።

ልሳኑ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# ርክበ ካህናት

ከጥንት ጀምሮ ብዙ የተለያዩ ጉባዔዎች አሉ ጉባዔዎችንም የሚፈጥሯቸው የተለያዩ ችግሮች ናቸው ። አንድ ሰው የገጠመውን ችግር ብቻውን ሊወጣውና ሊአቃልለው ከማይችልበት ሲደርስ ለቅርብ ጓደኛው ሐሳቡን አቅርቦ ከተነጋገሩበት በኋላ የመሰላቸውን መፍትሔ በውሳኔ መልክ ይሠነዝሩበታል ።

ገበሬ በእርሻው ፤ ነጋዴ ስለወረቱና ትርፉ የጅ ጥበበኛው ስለ ሚቀርጸውና ስለሚአነጥረው ፤ ይወያያል ።

ካህናትም ስለ ካህናት ተግባራቸው ርክበ ካህናት (ስብሰባ) አድርገው ይነጋገራሉ ። ማንኛውም ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ሰባዊ አካሉን በተፈጥሮ ላይ አስደግፎ ስለሚኖር በዓለማችን ላይ ካሉት የሥነ ፍጥረት ተግባራት ላይ ባንዱ ራሱን ያስማራል ።

ቢፈልግ ገበሬ፣ ነጋዴ ፤ አናጺ፣ አንጥረኛ፣ መድኃኒት ቀማሚ ወዘተ - - - ሊሆን ይችላል ስሙ ግብሩን እንደሚተረጉመው የካህናትም የስማቸው አጠራር ትርጉማቸው ይሆናል።

ካህን የሚለው ቋንቋ አማርኛ ወይም ግዕዝ ሳይሆን ዕብራይስጥ ነው ሳይለወጥ ካህን የሚለው ቃል ወደ ግዕዝ ሲቀላቀል አባቶቻችን ሊቃውንት ተክህነ የሚለውን ግሥ ፈጥረውለት ካህንን ዘር በማድረግ ቀላቅለውታል። ይሁን እንጂ ታሪኩን ስንከተል ይህ ቋንቋ ከዕብራይስጥ ፈልሶ መጥቷልና መንፈሱ እንደሚጠቁመን ካህን ማለት ሁለት የሥራ ጠባይ ያለበት መሆኑን አጉልቶ ያሳየናል ።

አንደኛው የኅብረተ ሰቡን ችግር በራሱ ተሸክሞ ከፈጣሪው ጋር ተገናኝቶ መፍትሔ የሚአስገኝ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ስለ ሕዝቡ ችግር ራሱን መስዋዕት በማድረግ ለሕዝቡ ጽድቅ አንድነት ሰላምና ነፃነት የሚቆም ማለት ነው ።

የቀደሙት ካህናት ይህን ስም የሚቀዳጁት በገዛ ፍላጐታቸውና በቤተ ሰብ ግፊት ሳይሆን በዚህ ሥራ እንዲሠማሩ ከእግዚአብሔር ጥሪ ሲደርሳቸው ብቻ ነበር ።

የሚጠሩትም በፈጣሪና በሕዝቡ መካከል አንድ ዓይነት አለመግባባት ሲፈጠር የሕዝቡን አቋም እንዲአስተካክሉ ነው ።

በዚህ ዓይነት የተጠሩትም ካህናት ጥሪውን ተቀብለው ራሳቸውን ከዓለም ምኞት አገልለው ለሕብረተ ሰቡና ለአምላክ ይቆማሉ ።

ከነሙሴ ጀምረን እስከ ክርስቶስ ያሉትን ካህናት ስንመለከታቸው ጥሪውን ተቀብለው ትክክለኛ ትርጉሙን በግብራቸው ገልጸዋል ።

ሙሴ እውነተኛ ካህን በመሆኑ የፈርዖን ልጅ መባልን ሳይቀበል ከድሆች ወገኖቹ ጋር የሚሳተፈውን መከራና ሥቃይ መረጠ ።

ጌታችን ኢየሱስም የካህናት ጠሪና ሿሚ በመሆኑ ትህትናን ጸዋትወ መከራን ከአደም ልጆች ጋር ተሳተፈ ።

አሮንና ልጆችም በእግዚአብሔር ተጠሩ (ዘጸ ፳፰ ፣ ፩—፫ ነገር ግን ከሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር በክህነታዊ አቋሙ ተሳስቶ ያልተነቀፈ የለም።

የሙሴን ሕይወት ብንወስድ የማስተዳደሩን ሥልጣን ብቻውን ሰብስቦ በመያዙ የዮቶር ኃይለኛ ነቀፌታ ነቅፎታል ዘጸ ፳ ፣ ፫—፳ ሙሴ ግን አስተዋይና ብዙም ጥቅምና ሥልጣን ያላማታው በመሆኑ ወዲያውኑ የዮቶርን ሂስ በመቀበል ማኅበሩን ሁሉ ወደ መገናኛው ድንኳን ሰብስቦ ስለመንፈሳዊ ሥራው ሰባ ሊቃውንትንና እነ አሮንን እየሰበሰበ መወያየት ጀመረ ።

እንግዲህ የካህናት ስብሰባ ረዥምና አጭር ፤ ዝርዝርና አጠቃላይ አቅዶች አሉት ፤ አቅዶችም ገና ወደ እምነቱ ውስጥ ያልገቡትን እንዲገቡ የሚአዘጋጅና ቀደም ብለውም ራሳቸውን ወደ እምነቱ ውስጥ ያስገቡትን ሰዎች በእምነታቸው አንጻር አቋማቸውን እንዲአጠናክሩ ሲሆን ፤ አጠቃላይ ዓላማው ግን ሁሉንም አጠቃሎ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር ማድረግ ነው።

በዘመነ ሐዲስም ዝርዝር ዓላማውን ስንመለከት የእግዚአብሔር ካህናት የሚሰበስቧቸው ፫ ዓበይት አጀንዳዎች ናቸው ።

## ስለ ሃይማኖታቸው ጥራት

ከጊዜ ጋር የማይሄደውን ከባድ ሥርዓት ማቃለል ፤ ካህናት የሚሆኑትን ራሳቸውን ከደው ለኅብረተሰቡ የሚቆሙትን ሰዎች ለመምረጥ ነበር ። የሐዋ ፲፩ ፣ ፮—፳፮

በስብሰባቸውም ላይ በጋለ መንፈሳዊ ስሜት ይከራከሩና ተገቢውንና ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድገት የሚሰጠውን ውሳኔ ያሳልፉ ነበር ።

በጴጥሮስ ሊቀ መንበርነት ትመራ የነበረችው ገና በሙሽርነት ብቅ ያለችው ርክበ ካህናት በመካከሏ አስቸጋሪ ውዝግብ ተፈጥሮባት ነበር።ይህም ሥርዓቱና ጊዜው ካለፈበት ከአሪት አንዳንድ ሐሳቦችን እያስገቡ ሊበርዟትና ሊቀላቅሏት አንዳንድ ሰዎች ተነሱባት ።

በዚህም ምክንያት ቅራኔው እየሰፋ በመሄዱ ከንኡስ ጉባዔ ጳውሎስና በርናባስ ወደ አጠቃላይ ጉባዔ ቀርበው የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲአስወስኑ ተላኩ ።

በዚህም መነሻ ሐዋርያት ከፍተኛ ስብሰባ አድርገው ብዙ የሐሳብ ለውጥ ከተካሄደ በኋላ ፤ ጴጥሮስ ፤ ጳውሎስና በርናባስ በተራ እየተነሱ አጠቃላዩ ጉባዔ ወደ ውሳኔ ይደርስ ዘንድ ድምጻቸውን አሰሙ ።



በመጨረሻውም የጉባዔው ድምጽ ባንድ ተጠቃሎ ለዚህ ቦታ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት የሚችሉትን ሰዎች ለመምረጥ ከፍተኛ የመመዘኛ ነጥቦችን አዘጋጅተው ይህ የኔ ያገሬ ተወላጅ ነው ይህ የከሌ ልጅ ነው ይህኛው ደግሞ እገሌ ያሳደገውና ከሁላችን ጋር የኖረ ነው ሳይሉ ፤ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የራሳቸውን ጥቅምና ክብር ከደው ሕይወታቸውን በመስቀሉ ሥር ያደረጉትን ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ሌሎችን ቅዱሳን መልእክተኞች ለመላክ ወሰኑ ። የሐዋ ፲፩ ፣ ፩—፩ጻሚ

የካህናትን ስብሰባ መሠረታዊ ታሪክ ከብሉይ እስከ ሐዲሱ ያለውን ባጭሩ ተመልክተናል በዚህ አንጻር የኛ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ስብሰባ ሲካሄድ ቆይቶ እንዴት ከዚህ እንደደረሰ እንመለከታለን ።

እንደተመለከትነው የካህን ሥራ በሁለት አቅጣጫ ሆኖ እግዚአብሔርን ወክሎ ከምዕመናን ጋር ፤ ምዕመናንም ወክሎ ከእግዚአብሔር ጋር መሥራት ነው ለዚህም ቅዱስ አገልግሎት ብቁ የሆኑትን የሚመለምላቸው እግዚአብሔር ሲሆን ሕዝቡም በክህነታዊ አቋማቸው በበቂ ችሎታቸው አምኖ«ይደልዎ»ብሎ ስለሚቀበላቸው ትዕዛዙና ቃሉ ተፈጻሚነት ሊኖረው ሲገባ በቤተ ክርስቲያናችን የሚታየው ሁኔታ ከዚህ ጋር ፈጽሞ ዝምድና አልነበረውም ሁኔታው ብዙ የሚያጠያይቀን ቢሆንም በመጠኑ ለማየት እንሞክራለን ።

ባለፉት ዘመናት የገዥው መደብ ቤተ ክርስቲያንን ለብዝበዛውና ለገፈፋው መጋረጃ ለወጡ የማግሚያ እንጨት አድርጓት ስለ ለጥቅሙ መስሪያነቷ ይረዳው ዘንድ ራሱን የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ አድርጐ ሾመ።

በእግዚአብሔር የተጠሩ ራሳቸውን ከግል ክብርና ጥቅም ይልቅ ለኅብረተሰቡ የቆሙ ካህናት ቢኖሩም ቤተ ክርስቲያን የወጥ እንጨትነቷን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመቃወማቸው እንደነዚህ ያሉትን እያሳደደና እያሰረ ሌሎችን ዓለማውያን ሰዎች ስለ ኅብረተ ሰቡ ደንታ የሌላቸውን በእግዚአብሔር ፈንታ እሱን የሚአመለኩትን ግለሰቦች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መኰልኰል ጀመረ ።

ቤተ ክርስቲያንም አላማዋን ስታ ሕዝቡን ከመሰብሰብና ከማስተማር ይልቅ ጢሰኛ አስፋሪና ከጢሰኛውም ቀረጥ ሰብሳቢ እንድትሆን ስላደረጋት ከምዕመናኑ ጋር ያላት ግንኙነት በጣም እየቀዘቀዘና እየላላ ሄደ ።

ለቅስናም ሆነ ለዲቁና አገልግሎት የሚመለመሉት ከላይ እንደተመለከትነው በእግዚአብሔር ጥሪ በሕዝቡ ፍላጐት ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከምዕመናኑ ጋር መሆኑ ቀርቶ ከመሬት ጋር የተቆላለፈ በመሆኑ በገጠር ይቀደስ የነበረ በባለርስቱና ባለሪሙ ስለሆነ ገንዘብ እንዳይጠየቅ ሲል ጋጠ ወጥ የሆነ ልጁን እያመጣ ያጉርበት ጀመር ።

በከተማም ለደብተርና ለልብሱ ራሱን ችሎ ወላጆቹን ሳያስቸግር እንዲማርና ለዓላማውዊ እድሉ እርካብ እንዲሆነው እየተባለ ለናቱና ላባቱ ቦርሳ ጠንቅ የሆነው የመንፈሳዊ መልክ የማይታይበትን ኪስ አውላቂውን ሁሉ አከማቹባት ።

በፊውዳል እየተመለመሉ የመጡት አባቶችም «እናንተ ጳጳሳት ራሳችሁንና እግዚአብሔርን በደሙ የዋጃችንን ቤተ ክርስቲያንን እንድትጠብቋት መንፈስ ቅዱስ ሹማችኋል» የተባለውን በመሳት ራሱ በዚህ ፋንታ ለመረጣቸውና ለሾማቸው ለገዥው መደብ ቆሙ ።

በዚህም ምክንያት በዚህ መልክ ለቀረባቸው ሁሉ የቅስናውንና የዲቁናውን ሥልጣን ነስነሱት ቤተ ክርስቲያንም የሌቦችና የቀማኞች ዋሻ ሆነች ።

እንግዲህ ከላይ ጀምሮ እስከ አፃዌ ኆኅት (በር ዘጊ) ድረስ ያሉት ሁሉ የዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ፍርፋሪዎች በመሆናቸው በየጊዜው የሚደረገው የስብሰባ ውጤት ሁሉ ፍርፋሪ እንጅ ከምጣዱ ጀምሮ የተጠበቀ እንጀራ ባለመሆኑ ቤተ ክርስቲያንን ሳያጠግባት ቆይቷል ።

ክርስቲያን ሁሉ የክርስቶስን ቃል በፍጹም ልቡ ከተቀበለ « ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ በተሰበሰባችሁበት ሁሉ እኔ በመካከላችሁ እገኛለሁ» ብሎ ነበር እንዴት ነው፤በቤተ ክርስቲያናችን ስብሰባ መካከል ተገኝቶ ሥራችንን የማያቃልልልን ብለን የምናስብ ጥቂቶች አይደለንም ።

ነገር ግን የጥቅሱን አገባብ በመልኩ ካልተመለከትነው ልንሳሳት እንችላለን ። ምክንያቱም በክርስትና አንጻር ስንመለከተው እግዚአብሔር እገኛለሁ ያለው በስሙ በተሰየመው የካህናት ስብሰባ መካከል እንጅ ለመሬት ከበርቴው ድጋፍና አጠናካሪ ሐሳብ ሰጭ ጉባዔ ላይ አልነበረም በዚህም ከንቱ ጉባዔ እግዚአብሔር ፈጽሞ እንደማይገኝ ግልጽ ነው ።

«ያለኔ ምንም ምን ማድረግ አትችሉም»የሚለው ሕያው ቃሉ የማይታጠፍ ነውና ውሳኔው ሁሉ የግመል ሽንት ሆኖ ይቀራል ።

ስብሰባው ባለፈው ሥርዓት የነበረው ቤተ ክህነት የግብር ገቢ እድገትና ዝቅተኝነት ስለ አንዳንዱ የቅርብ ዘመዶች የደመዎዝ ዕድገትና የደረጃ መሻሻል ስለ ከተማ ቤት ኪራይ አሰባሰብ እንጅ እንደ ሐዋርያት ስብሰባ ፤ ስለ ወንጌል ስብከት እድገት ስለ ምዕመናኑ ጥንካሬና ጥራት ብቁ የሆኑትን ካህናት ለመመልመል አልነበረም ።

ከለውጡ ወዲህ ያለው ርክበ ካህናት ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ተብትቦት ከነበረው ከቡርዥዋው ሥርዓት ተላቆ የራሱን መንፈሳዊ ስብሰባ ያለምንም ተጽእኖ እንዲአካሂድ ሰፊ ዕድል አግኝቷል ።

ቢሆንም ባለው አንፃር የሚካሔድ ስብሰባ አድርጐ ስለ ወንጌል ስብከት ፤ ስለ ሰበካ ጉባዔ መቋቋምና መስፋፋት ስለ ሰባክያን ፍጹምነትና ጥራት ተወያይቶ ትክክለኛውን ውሳኔ እያሳለፈ ባለማስፈጸሙና ምሑራኑን ባለማቀፉ የተጫነው የፊውዳሉ መንፈስና ድቅስቅሱ ፈጽሞ እንዳለቀቀው ሆኖ ይታያል ።

ከለውጡ ወዲህ ያለው ርክበካህናት ግንካለፈውጊዜሁሉየተለየአቋምናአመራረጥ ኖሮት ከራሳቸው ክብርና ሥልጣን ይልቅ ለሰፊው ሕዝበ ክርስቲያን የቆሙትን ፤ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ድልድይ ሆነው ማገናኘት የሚችሉትን ለዘመናችን ርእዮተ

ተከታዩን በ፲፭ኛው ገጽ ይመል



www.ethiopianorthodox.org

# «የሴቶች ድምፅ በመገናኛ ዘዴ»

ሴቶች ይበልጡን በመገናኛ ዘዴ መሥራት የሚወዱት ለምንድነው ? በዚህ የሥራ ዓይነት ሴቶች የተለየ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱት ይኖር ይሆን ? በዚህ ሥራ የተሠማሩ ከአሥራ አራት አገሮች የተውጣጡ ሃያ ሁለት ሴቶች የሚገኙበት በአሠራር ላይ አንዳንድ ማሻሻያዎችን ለማድረግ በቤይሩት ከተማ ሉባኖን ከታኅሣሥ ፲፭—፲፱ ፲፱፻፸፫ ዓ·ም ስብሰባዎች ተደርገው ነበር ።

ስብሰባዎቹም የተደረጉት በዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ማደራጃና ማሠራጫ ማኅበር በዓለም ወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማኅበርና በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አዘጋጅነት ነው። ባወጡትም የጋራ መግለጫ የመገናኛ ዘዴዎች ተግባር በሰው ልጅ ላይ የሚደረገውን ነገር በሙሉ በትክክል ማንፀባረቅ እንጂ መሸፋፈን እንደሌለባቸው አስታውቀዋል ። ይህ በተለይ በሴቶች ላይ ስለሚደረገው የጾታ ልዩነትና ጭቆናም ይመለከታል።

በስብሰባው ላይ የተገኙትን በዓለም ክርስቲያናዊ የማገናኛ ማደራጃና ማሰራጫ ማኅበር የትምህርት ክፍል ዋና ኃላፊ ዘልማ አዎሪ ሲናገሩ « ሴቶች በቤተ ሰብ ኃላፊነት፤ በሕፃናት አሳዳጊነትና በሚደረግባቸው ድርብ ጭቆና በጣም የሚያሳስብና በቀላሉ የማይታለፍ ስለሆነ ዓለም በሙሉ ሊነጋገርበት የሚገባና ለዚህም ትግል ለሚያደርጉ ሴቶች ድጋፍ መስጠትና ማነቃቃት የሚያስፈልግ መሆኑን ጠቅሰዋል ቀጥለውም «ሴቶች መሠረተ ለውጦችን ለማምጣት በብዛት ወደ መገናኛ ዘዴዎች በመግባት መታገል እንደሚያስፈልጋቸው አትተዋል ።

እነዚህንም ጉዳዮች ለማጠናከር ጉባዔው በመገናኛ ዘዴ ድርጅቶች ላይ የሚሠሩትን ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩልነትን ለማግኘት ማሻሻል የሚያስፈልግ መሆኑን ሲያሳስቡ በዝቅተኛና በአገር አቀፍ ያሉትንም የመገናኛ ዘዴ ሠራተኞችን አበረታትዋል ።

አዎሪ ሲናገሩ ከመገናኛ ዘዴዎች ጥገኝነት ነፃ መውጣት፤በሦስተኛው ዓለም አገሮች እንደሚደረገውና ሲደረግም ለዘመናት እንደቆየው ባህላዊ ድራማ ሙዚቃና የመሳሰሉትን የኪነት ሥራዎች ተመጣጣኝ ያደርገዋል የመገናኛ ዘዴዎችን ሕዝቡከመስማትበቀርምንም መሥራት እንደማይችልና የፕሮግራም አዘጋጅዎች የሚያቀርቡትን መቀበል ብቻ እንዳለበት ያደርጉታል። የሦስተኛ ዓለም አገሮች ሴቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት ለብዙ ጊዜ የኖሩበትና የተካፈሉበት ስለሆነ በበለጠ የመሳተፍ እድል ይኖራቸዋል ።

ጉባዔው ሴቶች በመገናኛ ዘዴ አሠራር በቂ ዕውቀት እንዲያገኙ በስብሰባዎች ግን ጕነትን በመፍጠር የባህል ልውውጥ እንዲያደርጉና ብዙኃኑ የሚሳተፉበት የመገናኛ ዘዴዎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲቋቋሙ ለማድረግ በገንዘብና አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ እንዲረዱ የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ማሰራጫና ማደራጃ ማኅበርንየዓለም ወጣቶች ክርስቲያናዊ ማኅበርና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርን ይጋብዛል ።

ስብሰባውን በሊቀ መንበርነት የመሩት የኒዮርኩ የተባበሩት ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን የዓለም አቀፍ የትምህርት ቦርድ አባልና የሕዝብ ግንኙነት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ዶሪስ ኢሄስ ሲሆኑ ስብሰባዎቹንበታዛቢነት የተመለከቱት የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ማሰራጫና ማደራጃ ማኅበር ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ሃንስ ደልብ ዩፍሎሪንና የመካከለኛው ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ጠቅላይ ጸሐፊ ገብርኤል ሃቢብ ናቸው።

የጉባዔው ሪፖርተር ይቀጥላል

ብርሃን ተድላ

## ርክበ ካህናት

ከ፲፯ኛ ገጽ የዞረ

ዓለም ቀንድ እንጂ ጅራት የማይሆኑትን በጠቅላላው ስፍሐ አእምሮ ያላቸውን ሐዋርያት መልምሎ በነቃው ምዕመን መካከል እንዲያሠማራ በናፍቆት እንጠባበቃለን ።

ይህንም ማድረግ የሚችለው ዮቶር ለሙሴ በሰጠው መመሪያ ተጠቅሞ ለሥራው ተካፋይ የሚሆኑትን ሰባ ሊቃናትን መርጦ እንዳስገባ ሁሉ የእኛም ርክበ ካህናት ስብሰባ እንደ ሙሴ ሂስ ተቀባይ ሆኖ በቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ ትርጓሜ የታነጹትን በዘመኑም ፍልስፍና ራሳቸውን ያስተካከሉትን ወጣቶች ሲያቅፍ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ግን እንኳን ለተጠቃሚው ለተመልካቹ ብዙ ነገሮችን የተሸከመ ኩሬ ይሆናል ።

እንደ ቀድሞውም ርክበ ካህናት ዓላማውን ስቶ ጥራት የሌላቸውን ሸቀጦች ቢሰበስብ በቤተ ምኩራብ ገብቶ መደርደሪያውን ያፈረሰ የክርስቶስ ኃይል አልታጣፈም ሽፋሎችን ያስበረገገ የክርስቶስ ጅራፍም አልተጠቀለለምና ርክበ ካህናታችን ለትክክለኛው ሥራ የቆመ ከሆነ ቅዱስ ሲኖዶሳችን የውጭውን ዓለም ሲኖዶስ ሊከተል ይገባል የውጭው ዓለም ሲኖዶስ ከወጣቱ ፤ ከምእመናኑ ከካህናቱ ጋር አብሮ ስለሚሠራ ውጤቱ ክርስቲያናዊ ዓለም ዓቀፍ ሆኖ ይታያል የእኛም ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ ዓይነት ቢመራ መልካም የሥራ ውጤት እንደሚኖረው እናምናለን ።

አስተርአየ ጽጌ



# በጅማ ከተማ የተደረገው መንፈሳዊ የጥናት ጉባኤ (ሴሚናር) ተፈጸመ

ከወጣቶችናጉልማሶችመንፈሳውያን ማኅበራት፤ አጠቃላይ ስብከተ ወንጌል ማኅበር ቃልተቀባይእንደደረሰንበኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ መምሪያ እንዲሁም በወጣቶችና ጎልማሶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ ስብከተ ወንጌል ማኅበር የጋራ ጥረትና መንፈሳዊ ኅብረት ተዘጋጅቶ ከሚያዝያ ፳፰ ቀን እስከ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ·ም በጅማ ከተማ የተከናወነው መንፈሳዊ የጥናት ጉባኤ ( ሰሚናር ) በተሳካ ውጤት መፈጸሙን ከአዘጋጆቹ ክፍሎች በተሰጠው ጋዜጣዊ ዘገባ ተገልጧል ።

በዘገባው እንደተገለጸው የጥናት ጉባዔው (ሴሚናሩ) ዋና ዓላማ ፤

ሀ/ ካህናትና ምዕመናንን በሰበካ ጉባኤ

ለ/ ወጣቶችን በመንፈሳውያን ማኅበራትና የሰንበት ት/ቤት ለማቋቋምና ለማጠናከር ሲሆን የጥናት ጉባኤውን (ሴሚናር) የተካፈሉትም ፤

፩- የከፋና የኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ሊቃነ ካህናት (ሥራ አስኪያጆች)

፪- የሁለቱም ሀገረ ስብከት አውራጃ ሊቃነ ካህናት ፤

፫- ከሁለቱም አህጉረ ስብከት የተወከሉ ሰባኪያነ ወንጌል

፬- ከሁለቱም አህጉረ ስብከት የተወከሉ ሰበካ ጉባዔያት የተወከሉ ካህናትና ምዕመናን ፤

፭- በሁለቱም አህጉረ ስብከት ከተቋ



በጥናት ጉባኤው መጨረሻ የተቋቋመው የከፋ ሀገረ ስብከት የወጣቶችና ጉልማሶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ ስብከተ ወንጌል ማኅበር የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ከአጠቃላይ ስብከተ ወንጌል ማኅበር ምክትል ሊቀ መንበር ጋር ።



www.ethiopianorthodox.org

ጳሙት የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት የተወከሉ ወጣቶች

፮- ካልተቋቋመባቸው አብያተ ክርስቲያናት ለወደፊት የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ሊያቋቁሙ የሚችሉ ዲያቆናት የጥናት ጉባዔው ከሴሚናሩ መደበኛ ተሳታፊዎች ሲሆኑ በተለይ የጥናት ጉባኤው ከተካሄደበት ከጅማ ከተማ አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ በርከት ያሉ ካህናትና ዲያቆናት እንዲሁም ምዕመናን ከሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ጽ/ቤት አባሎች ጋር የጥናት ጉባኤው (ሴሚናሩ) ተሳታፊዎች እንደነበሩ ከተላለፈው ዘገባ ለመረዳት ተችሏል ።

በከፋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና መርሐ ጽድቅ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተገኝተው የጥናት ጉባኤውን (ሴሚናሩን) በጸሎተ ቡራኬና በንግግር የከፈቱት ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የከፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ መሆናቸውም ከአዘጋጆቹ በተላለፈልን ዘገባ ተገልጿል ። ሊቀ ጳጳሱ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በጥናት ጉባኤው (ሴሚናሩ ) ላይ መገኘታቸው በተሰጡት ትምህርቶች መነሻነት በአስተዳደር አንፃር የሚጠየቁት መጠይቆች በትክክል መልስ ሊያገኙ በመቻላቸው ከፍተኛ መግባባትና ስምምነት እንደነበር ተጠቁሟል ።

በጥናት ጉባኤው በተከታታይ የተሰጡት ትምህርቶች ፤

፩- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመምህር የማነ ብርሃን ተሾመ

፪- የሰበካ ጉባኤ ዓላማና ተግባር በአቶ አበራ በቀለ

፫- የሰበካ ጉባኤ ደንብ /ቃለ ዐዋዲ) ጥናት በአቶ አበራ በቀለ

፬- የካህናት ተልዕኮ በመልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን

፭- ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ድርሻ ቀደም ሲል በአቶ ሐዲስ ተረፈ

፮- የመንፈሳውያን ማኅበራት አቋምና አመሠራረት በዲያቆን ኃ/ጊዮርጊስ ዳኘ ከመስጣቸውም በላይ የቀበሌና ገበሬ ማኅበራት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ በስህተት ስለአደረሱት አንዳንድ ችግር በክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ድርጅት ተወካይ ለጥናት ጉባኤው ተካፋዮች ገለጻ ተደርጓል በተጠየቁትም ጥያቄዎች ተገቢው መልስ በተወካዩ የተሰጠ ሲሆን የሰበካ ጉባኤ ያትና የመንፈሳውያን ማኅበራት ችግርና መፍትሔው በሚል ርእስ ሰፋ ያለ ጥናትና ውይይት ተደርጓል ፤

ለዚህም ጥናትና ውይይት መልካም አጋጣሚ የነበረው በጥናት ጉባኤው መጀመሪያ በጅማ ደብረ መዊዕ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የጥናት ጉባኤው ፍጻሜ ዕለት ደግሞ በጅማ ደብረ ሰላም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተሳታፊዎቹ በማስቀደሳቸው የተደረገላቸው መልካም አቀባበልና መስተንግዶም ነው ።

ይህ ዓይነት የጥናት ጉባኤ ( ሴሚናር) ሲደረግ አሁን ሦስተኛ ጊዜው ቢሆንም በጅማ ከተማ የተደረገውን የጥናት ጉባኤ (ሴሚናር) ለየት የሚያደርገው ፤

፩- የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደድሮው ወደ ላይ ማንጋጠጣቸውን ትተው በራሳቸው ላይ ውሳኔ ማሳለፋቸውና የጥናት ጉባኤውን (ሴሚናሩን) በሥራ ለመተርጐም ከሀገረ ስብከቱ ጋር በመተባበር የሚሠራ አንድ ሥልጣን ያለው ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊቋቋም መቻሉ ሲሆን ፤

፪/ በከፍተኛ ጥረት በልዩ ልዩ ሰበብ ተለያይተው የነበሩት ያከፋ ክፍለ ሀገረ ስብከት ወጣቶች አጠቃላይ ስብከተ ወንጌል ማኅበራቸውን ሊመሠርቱ መቻላቸው ደግሞ የጥናት ጉባኤ ( ሴሚናሩ ) ተጨማሪ የመጀመሪያ ውጤት ነው ።

ከኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ተወጣጥተው የመጡት ወጣቶችም ከክፍለ ሀገራቸው እንደደረሱ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ካህናት (ሥራ አስኪያጅ) አስተባባሪነት አጠቃላይ ስብከተ ወንጌል ማኅበራቸውን መሥርተው ውጤቱን በአፋጣኝ ለዋናው አጠቃላይ ስብከተ ወንጌል ማኅበርና ለወጣቶች ጉዳይ መምሪያ እንደሚገልጹ በጉባኤው ፊት ቃል መግባታቸው ታውቋል ።

ከአዘጋጆቹ የተላለፈልን ዘገባ ሐተታውን ሲያጠቃልል የከፋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ጽ/ ቤት ሠራተኞች ካህናትና ምዕመናን ስለአሳዩት ከፍተኛ የሥራ ትብብር ከልብ አመስግኖ ይህን ዓይነቱ የጥናት ጉባኤ (ሰሚናር) በተከታታይ ለቤተ ክርስቲያናችን ጠቃሚ መሆኑን በመግለጥ ለዚህ ዝግጅት በሐሳብና በሞራል የተባበሩትን ሁሉ አመስግኖዋል ።

የቤተ ክርስቲያናችን ተወካይዎች ለዚህ የጥናት ጉባኤ የተሰበሰቡት ከኢሉባቦር ሀገረ ስብከትና ከከፋ ሀገረ ስብከት አውራጃዎች በመውጣጣት ስለሆነ የእናት አገር ጥሪን ለማስተባበርም ከፍተኛ ዕድል ነበረ የከፋ ክፍለ ሀገር የሕዝብ ድርጅት ሊቀ መንበር — በዚህ ጉባኤ ላይ በመገኘት ሰፋ ያለ ትምህርት በመስጠታቸው የሰሚናሩን ጠቃሚነት አስረድተው አመስግነዋል ።

ይህ ለሦስተኛ ጊዜ በጂማ ከተማ የተፈጸመው ከፍተኛ ሐዋርያዊ ጉዞ ምዕመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንንም ወደ ምዕመናን የሚያገናኝ ድልድይ መሆኑን የተገነዘቡ ምዕመናን ብዙኃን ነበሩ ።

ስለዚህም መልካም አገልግሎት በማንኛውም ማቴርያል ለተባበሩ ሁሉ የኢት/ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ በዚህ አጋጣሚ ምስጋናውን አቅርቧል ።



# ሁሉም ድርሻውን ሲያበረክት


(ካለፈው የቀጠለ)

ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት ማለት የየቤተ መቅደሱ አስተዳዳሪዎች፤ቀሳውስት፤ ዲያቆናት፤ መዘምራን መምህራን እንዲሁም በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ተመድበው የሚሰሩት ሁሉ በጦርነቱ ተሳታፊ ሆነው ግዳጃቸውን ፈጽመዋል አሁንም በመፈጸም ላይ ይገኛሉ ካህናቱ የፈጸሙት አገልግሎት በሁለት አንፃር የሚታይ ነው ይኸውም በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለውን መንፈሳዊ አገልግሎት ያለማቋረጥ ሲፈጽሙ ሀገርን ቆርሶ ለመውሰድ የመጣውን ወራሪ ጠላት ለመደምሰስ በሚደረገው ትንንቅ ከሠራዊቱ ጐን በመሰለፍ ለሠራዊቱ ሞራል በመስጠት በጦርነቱም ተሳታፊ ሆነው ተገኝተዋል በአደረጉትም የቆራጥነት ተጋድሎ አብዛኛዎቹ ካህናት ከክፍለ ሀገሩና ከአውራጃዎች ባለሥጣልኖች ከፍተኛ የምስጋና ቃል ተሰጥቶአቸዋል ከክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ጽ/ቤትና እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታተው ክፍል የመጣውን ጠላት ለመደምሰስ በሚደረገው ወይም በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ካህናቱ ባለመለየት አብረው ከሕዝቡና ከሠራዊቱ ጋር በመሰለፍ ለሀገር የሚገባውን ግዳጅ ፈጽመዋል ወደፊትም ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይሉ ግልጽ ነው በሀገር ቀልድ የለምና ።

በዚሁ ወራሪ የቀብሪ ደሐር ቅድስት ማርያም አስተዳዳሪ የነበሩት ጅጅጋ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ያገለግሉ የነበሩት መንፈሳውያን አባቶች እዚያው ሕይወታቸው በጠላት እጅ ያለፈ ሲሆን የፈዲስ ወረዳ ቤተ ክህነት ሹም የነበሩት መምሬ አባተ በጠላት ታፍነው ተወስደዋል የከምቦልቻ ወረዳ ቤተ ክህነት ሹም የነበሩትም ከጠላት ጋር በሚደረገው ትንቅንቅ ላይ እንዳሉ ሕይወታቸው አልፎአል ለማስረጃ ያህል እነዚህን ጠቀስኩ እንጂ በዚህ ጦርነት ብዙ ካህናት ሕይወታቸውን ሰውተዋል የቀብሪ ደሐር ቅድስት ማርያም የጅጅጋ ቅዱስ ሚካኤል የተፈሪ በር ሥላሴ የግሪ ቆጪር ቅድስት ማርያምና እነዚህን በመሳሰሉት ወራሪው ጠላት በደረሰባቸው ስፍራዎች የነበሩትም ካህናት ከሰራዊቱ ከሕዝቡ ባለመለየት በጦር ግንባር በመሰለፍ ከፍተኛ ግዳጅ ፈጽመዋል ።

በሀገረ ስብከቱና በወረዳና በአውራጃ የሚገኙቱ የቤተ ክህነቱ ሠራተ

ተከታዩ በ፳፪ኛው ገጽ ዞሯል



በምሥራቃዊና በደቡባዊ ክፍላት ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች ።



www.ethiopianorthodox.org

# በበዓለ ሃምሳ ያሉት ረቡዕና ዓርብ ለምን ይበላሉ ?

## በመጀመሪያ የምንጾምበትን ምክንያት እንገልጸለን

ለማናቸውም ተግባር ሁሉ መመሪያ አለው መመሪያ የሌለው ሥራ ግቡን አይመታምና ፣ እንደዚሁም ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበትን መመሪያ አውጥታ ዕለትና ሰዓት ወስና ትመክራለች ታስተምራለች።

ከብዙዎችም መገናኛዎች አንዱ ጾም ነው ይህም ጾም በአምላክ ፈቃድ ለሰው ልጆች የታዘዘና የተሰጠ ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለኛ ያደረገልንን ቸርነት በሥራ ገልጦ ሲአስተምረን የመጀመሪያው ተግባር ጾምና ጸሎት ነው።

አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ፣ጸለየ ሌሎችንም አስተማረ ማቴ- ም-፬ ቁ፣ ፱ ቁ፣ ፲፰ ለሁሉም መመሪያ አለው እንዳልነው ሁሉ ለዚህ ለተቀደሰ አላማ አባቶች አንድ አንቀጽ ስተውታል ከሰባትም ከፍለውታል ከሰባቱም አንዱ ዓርብና ረቡዕ ናቸው ።

የስድስቱን አጽዋማት ሁኔታና ዘርፎች ከአስረዳን በኋላ «አዲ ረቡዓ ወአርበ በዡሉ ሱባዔ ዘእንበለ መዋዕለ ፶ ወበዓለ ጥምቀት ሶበ ኅብሩ በሙ»ይህም ማለት ልደት፣ጥምቀት፣በዓለ ሃምሳ ካልዋሉባቸው በስተቀር በየሳምንቱ ዓርብና ረቡን መጾም ይገባል አርባ ጾምንና አርብና ረቡን የማይጾም ክርስቲያን ካህን ቢሆን በክህነቱ ምዕመንም ቢሆን በምዕመንነቱ ይመከር ይቀጣ አልመለስም ቢል ይለይ የታወቀ ደዌ ያለው ከሆነ ግን በደዌው ምክንያት ነጻ ነው። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፭ አርብና ረቡዕ የሚጾምበትም ምክንያት ረቡዕ የምንጾምበት የዓለም መድኃኒት ክርስቶስን መድኀኒትነቱን ያላመኑ አይሁድ ለመግደል ፤ የጭካኔና የግፍ ምክራቸውን ያጸኑበት ዕለት ስለሆነ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት እንድናስታውሰው ቤተ ክርስቲያን በሕግ አድርጋ ሠርታልናለች። ሁለተኛም ዓርብ ለዓለም የተገረነው ተስፋ ሲፈጸም እርቃኑን አድርገው በመስቀላይ እጁን ዘርግቶ ደሙን ሲያፈስ ሥነ ፍጥረቶች ሌላ መልክ አሳይተዋል በተለይም በሰማይ ፫ በምድር አራት በድምሩ ሰባት ተአምራት ተፈጽመዋል ፀሐይና ጨረቃ ብርሃናቸውን ነሥተው ጻመና-ጨለማ ሁነዋል ከዋክብትም ረግፈዋል በምድርም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከሁለት ተሰንጥቋል መቃብራት ተከፍተዋል ነፍሳት ተነሥተዋል አዕባን ተፈትተዋል ይህ ሁናቴ የሚአመለክተን የመከራና የኃዘን ዕለት መሆኑን ነው ስለዚህ በየሳምንቱ እኒህን ሁለቱን ዕለታት የምንጾምበት ምክንያት በዚህ ነው በየሳምንቱ ሁለት ቀን ጾም እንዳለ ሉቃስ በምዕራፍ አስራ ስምንት በቁጥር ፲፪ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወ

ተከታዩን በ፳፱ኛው ገጽ ይመልከቱ

# ሁሉም ድርሻውን ሲያበረክት

ከ፳፩ኛው ገጽ የዞረ

ኞችም መንግሥት በሚያደርገው ጥሪ መሰረት እየተገኙ ትጥቅ በመቀበል በጦር ግንባር ተሰልፈው ውለዋል ። በሀገረ ስብከቱ የሚገኘውን የጽሕፈት ቤቱን ሥራ ለጊዜው በቁልፍ የሥራ መደብ ላይ ያሉት ተላላኪነቱን ጭምር በማጣመር እየሰሩ ቆይተዋል በዚሁ የጦር ግንባር የሀገረ ስብከቱ የየመምሪያው ኃላፊዎች ሳይቀሩ ተሰልፈዋል።

እንዲሁም የሰብል ስብሰባ ዘመቻ በተደረገ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የሚገኙት ሠራተኞችና በሙሉና በአድባራቱ የሚገኙት ካህናት ከክፍለ ሀገሩ በተሰጠው መመሪያ መሠረት በሰብል ስብሰባው ላይ ተገኝተዋል በጦርነቱም ሆነ በሰብል ስብሰባው የራስ መኰንን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መምህራን አብረው ተገቢውን የሀገረ ግዳጅ ፈጽመዋል በሀገረ ስብከቱና በራስ መኰንን መንፈሳዊ ት/ቤት የሚገኙት ሠራተኞችና መምህራን የመጣውን የሱማሊያ አድኃሪ መንግሥት ወታደር የማያዳግም ቅጣት ለመስጠት በታጠቁት መሳሪያ ተገቢውን ቅጣት ሰጥተውበታል ። አሁንም በእጃቸው አለ ።

በካህናቱም እጅ ያለው በዚሁ ዓይነት ይገኛል ተሰዶ የነበረው ሕዝብ አሁን ወደቀደመው ስፍራ በመመለስ ላይ ያለ ሲሆን ካህናቱም ከሕዝቡ ባለመለየት ወደቀድሞ ስፍራቸው በመመለስና ሕዝቡን በማጽናናት ላይ

በቁልቢ አካባቢ ለአንድ ቀን ተደርጎ በነበረው ጦርነት በየጊዜው በሚደረገው አሰሳ የዚሁ ደብር ካህናትና ሠራተኞች ከሕዝቡና ከሠራዊቱ ጋር አብረው ተሰልፈው ግዳጃቸውን በተገቢ ሁኔታ ፈጽመዋል ። በአጠቃላይ በሐረርጌ ክፍለ ሀገር የሚገኙት ካህናትና መምህራን እንዲሁም በአውራጃና በወረዳ በሀገረ ስብከቱ የሚገኙት ሠራዊትና ከሕዝቡ ባለመለየት ተገቢውን የሀገር ግዳጅ ፈጽመዋል ወደፊትም ከሕዝቡና ከሠራዊቱ ባለመለየት ከቀድሞው ይበልጥ የሚሰለፉ ናቸው።



# የመጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር ዓምድ

## የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያቸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ፍርሃት ፤ ጭንቀት ነበረባቸው። ነገር ግን በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር። የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ይጸልዩ ነበር። አምላካችንም ከልብና በእውነት ለሚጠሩት ቅርብ ስለሆነ ሁኔታቸውን ተመልክቶ መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው ኃይልንም ሞላባቸው ። ብዙዎችንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለማምጣት አበቃቸው። ይበልጥ ለመረዳት የሚከተለውን ቃል በእርጋታ ይመርምሩ ። የሐዋ ፣ ሥራ ፣ ፪፡፩—፳፩ ።

በዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፤ ሀ ሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፤ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው ፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጠባቸው ። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር ።

ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ ፤ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለ ነበር የሚሉትን አጡ። ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ « እነሆ ፤ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን? የጳርቴና የሚድ የኢላሚጤም ሰዎች፤ በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጰዶቅያም በጳንጦስም በእስያም በፍርግዷያም በጵንፍልያም በግብፅም በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር በሮሜም የምንቀመጥ ፤ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን፤ የቀርጤስና የዓረብ ሰዎች፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። ሁሉም ተገረሙና አመንትተው እርስ በርሳቸው እንጃ ? ይህ ምን ይሆን ? አሉ ። ሌሎች ግን እያፌዙባቸው ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ ።

ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ ። ድምጹንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው ፣ አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ ፤ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን ቃሎቼንም አድምጡ ። ለእናንተ እንደመሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፤ ከቀኑ ሦስት ሰዓት ነውና ፤ ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው ። እግዚአብሔር ይላል'—በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል « ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ ፤ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፣ ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ።ድንቆችን በላይ በሰማይ፤ ምልክቶችንም በታች በምድር እሰጣለሁ ፤ ደምም እሳትም የጢስ ጭጋግም ይሆናል ፤ ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደደም ይለወጣሉ ። የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል ።

ብሏልና ስሙን በመጥራትና መልካም ሥራ በመሥራት እርሱን እንከተለው ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
የፖ. ሣ. ቁጥር 30750
ስልክ 122033
አዲስ አበባ
የፖ. ሣ. ቁጥር 700
ስልክ 113455
አሥመራ



www.ethiopianorthodox.org

# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና

ኢትዮጵያ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ግንቦት ፲ ቀን ፸ ዓ-ም ወደ መስኮብ ሔደዋል ።

ከቅዱስነታቸው ጋር የሔዱት ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጐጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት የበላይ ተጠሪ እንዲሁም የልማት ኮሚሽን ሥራ አስፈጻሚ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የከፋ ክ/ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅ/ሲኖዶስ ጸሐፊ ዶክተር አባ ሀብተ ሥላሴ ተስፋ የቤተ ክህነት የውጪ ጉዳይ አላፊና መምህር ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ አብረው ሄደዋል ።

★ ★ ★

ኢትዮጵያ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ከሚያዝያ ወር ፲፱፻፸ ዓ-ም ጀምሮ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ከባሌ ወደ ጐጃም ሀገረ ስብከት፤ ብፁዕ አቡነ ማርቆስን ወደ ባሌ ሀገረ ስብከት ያዘዋወሩአቸው መሆኑን ዜና ቤተ ክርስቲያን ገለጸ ።

✶ ✶ ✶

ናሚቢያ ፤ የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት በናሚቢያ ሊቋቋም ነው ።

በዚህ ዓመት በጥር ወር መጨረሻ ላይ የሉተራን የካቶሊክ፤ የአንግሊካን፣ ኮንግሪግሽናልና የአፍሪካን ሜቶዲስት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች አንድ አጠቃላይ ስብሰባ አድርገው ፤ የናሚቢያ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ለመመሥረት ተስማምተው ለዚህም የክርስቲያኖች ኅብረት ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፸ ዓ-ም- የጸሎት ቀን አድርገውት ውለዋል።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ፊሊፕ ፓተር ይህንኑ አስመልክተው ለመሥራቹ ኮሚቴ ሊቀመንበር ባስተላለፉት መልእክት፤

ተከታዩን በ፳፭ኛው ገጽ ይመልከቱ

# በበዓለ ሃምሳ ያሉት ረቡዕና ዓርብ ለምን ይበላሉ ?

ከ፳፪ኛው ገጽ የዞረ

ጣለሁ ሲል የተናገረውን ገልጦልናል ።

ታሪኩ እንዳይበዛ በማለት ነው እንጂ በብሉይ ኪዳን የነበሩ አበውም ከሳምንትሁለት ቀን ይጾሙ እንደነበር ታሪክ ያስተምረናል መጽሐፍ ቅዱስም ይነግረናል ዓርብና ረቡዕን በሌላው ቀን የምንጾማቸው ምክንያት ከዚህ በላይ የተገለጸው ነው።

በበዓለ ሃምሳ ውስጥ ያሉትን የማን ጾምበትን ምክንያት ግን ከዚህ ቀጥለን እንገልጣለን። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀበት እስከሞተበት ያሉትን፤ዘመናት ሁሉ በመራብ ፤ በመጠማት፤በመወንጀል፣በመታሠር፣በመገረፍ በመሰቀል በመሞት ከአሳለፈ በኋላ በሱም ሞት ሲአዝኑና ሲጨነቁ ለነበሩት ደቀ መዛሙርት ሞትን በሞት ሽሮ ማለት የሰይጣንን መንግሥት ደምስሶ ተሰብስበው ሲጨነቁ ለነበሩት በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለናንተ ይሁን አላቸው የሉ- ፳ ቁ-፲፱ ሉቃ-፳፳ ቁ- ፴፮ ይህ ሰላምና ደስታ የተገኘበት የዲያብሎስ መንግሥት የተደመሰሰበት ዘመን ስለሆነ አምሳውን ዕለታት ሁሉ ክርስቶስ እንደተነሣባት ዕለት ተቆጥረው የደስታ የዕረፍት ዕለታት ይሆኑ ዘንድ ቤተ ክርስቲያናችን ወስናለች ልደት፤ጥምቀት በዓለ ሃምሳ ከሚ ውሉባቸው በስተቀር ያለው ስለዚህ ነው ። ይህውም አምሳውን ቀን ሁሉ ከእሑድ ለየት ያለ መልክ የምንሰጠው በሥራ ነው ማለት እኒህ ሁሉ እለታት ከሥራ ከተከለከሉ በሕዝብ ላይ ጉዳት ስለሚደርስ ሥራውን እየሠሩ ፈጣሪአቸውን በነግህ፤በቅዳሴ፣ በማኅሌት በመዝሙር ከአመሰገኑ በኋላ አርብ ነው ረቡዕ ነው ሳይሉ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ከጾም ከስግደት ከቀኖና ተከልክለው የሚወዱትን መብል መጠጥ ሳይከለከሉ ደስታቸውን ይፈጽማሉ ምክንያቱም በጾም፣በጸሎት ፤ በስግደት በቁመት፤በሀዘን ሲቀጠቀጡ የቆዩ ስለሆነ የመከራ አጸፋው ደስታ ነውና የልደትና የጥምቀትን አርብ ረቡዕ በገሃድ ለውጥ ነው የበዓለ ሃምሳውን በምን መልክ ነው የሚል ጥያቄ ቢኖር መልሱ ይህ ነው በመጀመሪያው ሱባዔ እስከ ፲፪ ሰዓት በሁለተኛው ሱባዔ ማለት ከቅድስት እስከ ኒቆዲሞስ ፲፭ ሰዓት ሕማማትን ከሌሊቱ አንድ ሰዓት ጨምሮ ፲፫ ሰዓት ይጾማል በሌላው ጊዜ ያት ያሉት አጽዋማት ግን የሚጾሙት ፱ ሰዓት ነው ከዚህ ላይ ግን ከዘጠኝ አብልጠን የጾምናቸው በሃምሳው ውስጥ ላሉት ዓርብና ረቡዕ ገሃድ ወይም ተውላጥ ናቸው ከዚህም ሌላ ክርስቶስ በመስቀል ላይና በመቃብር የቆየበትን ብለን እንመልስለታለን ቅዳሜ ሥዑር የተባለችውን ዕለት ጭምር በመጾም በአክፍሎት የተገኘው የክርስቶስ ዕለተ ትንሣኤ ሃምሳው ቀን እንዳንድ ዕለት ሊቆጠር ቻለ ። ስለዚህም ባጠቃላይ አምሳው ዕለታት ሊታዘንባቸው ሊጾምባቸው የማይገቡ ለደስታ ብቻ የተመደቡ ስለሆኑ እንጾማቸውም ።

መምህር መርሐ ጽድቅ ገብረ ሕይወት





ከ፳፬ኛው ገጽ የዞረ

ደስታቸውን የገለጹ ሲሆን ቀጥለውም ሲናገሩ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት አማኞች እንዲሰበሰቡና በአንድነታቸውም ፍሬ እንዲያደሰቱ ማድረግ ተግባራችን ጭምር ነው ሲሉ በመልእክታቸው ጠቅሰዋል ።

ለዚሁ ለሚመሠረተው የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት የተዘጋጀው የመተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን ዓበይት ነጥቦች ይዟል ። የእግዚአብሔር ፈቃድና ስጦታ የሆነውን አንድነትን መንከባከብ ፤ በአብያተ ክርስቲያናቱ ጉባኤ ከስምምነት የተደረሰበትን የአብያተ ክርስቲያናትን እንቅስቃሴዎችንና ተግባራትን ማጠናከር ፤ አብያተ ክርስቲያናቱን የሚያገናኟቸውን ጉዳዮችና ፍላጐቶች ማጠናከር፤ ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ለመርዳት የሚያቋቁሙትን ፕሮጀክቶች ወይም የሥራ ድርጅቶችን መርዳት የዚሁኑ ዓይነት ዓላማ ካላቸው ክፍሎች ሁሉ ጋር መተባበር የናሚቢያን አብያተ ክርስቲያናት የሚመለከቱ ዜናዎችን ማሰራጨት ፤ ደግሞም ከውጭ እነዚህኑ አብያተ ክርስቲያናት የሚመለከቱ ዜናዎችን መሰብሰብ ፤ የውይይት ጉባዔዎችን ትምህርታዊ ኮርሶችንም ማደራጀትና መምራት የሚሉ ናቸው ።

ምንም እንኳን ዘረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ናሚቢያን ለቆ እንዲወጣ በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ቢደረግበትም በአሻፈረኝ ባይነት አሁንም እዚሁ ይገኛል ። ከዚህም ዘረኛ መንግሥት ግፍና በደል የተነሣ አደጋ የሚያደርስባቸውንም ሆነ የሚታሰሩትን ሁሉ አብያተ ክርስቲያናቱ በኅብረት ርዳታቸውን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ ። ከዚህ በጐ አድራጐት ተግባር የተነሣ ብዙ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ተሰደዋል ። በዚሁ ረገድ፤ በ፲፱፻፷፯ ዓ-ም- በናሚቢያ የደማራላንድ አንግሊካን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሪቻርድ ውድ በአገሪቱ ባለሥልጣኖች ተባረዋል ። ሊቀ ጳጳሱ የተባረሩት ስለተጨቆኑት ዜጐች በመከራከራቸውና ራሳቸውን ከነርሱ ጋር በመቁጠራቸው ነው ሲል ኢ-ፒ-ኤል የተባለው ኤኩሙኒካል መጽሔት በሚያዝያ ፲፱፻፸ ዓ-ም እትሙ ገልጧል ።

✶ ✶ ✶

ፊንላንድ ፤ በሰሜን አውሮጳ በምትገኝ በፊንላንድ ፤ በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የሚዘጋጅ «የቤተ ክርስቲያን ቀናት» የተባለ ልዩ መንፈሳዊ በዓል እንደሚደረግ የሚያዝያው ወር የዓለም ሉተራን ፌዴራሲዮን መጽሔት አስታወቀ ።

ይህ መንፈሳዊ በዓል ከሰኔ ፲፱፻፸፩ ዓ-ም የሚከበር ሲሆን የበዓሉም መመሪያ ቃል «እንደክርስቲያን ለመኖር አዲስ ኃይል» የሚል ሁኖ በዓሉ በሚከበርባቸው ቀናት ስለአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነቶች ውይይት ይደረጋል። ይህም የአብያተ ክርስቲያናት ውይይት «ከቅራኔ ወደኅብረት» ይሆናል።

ስለዚሁ በዓል በፊንላንድ የአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ጠቅላይ ጸሐፊ በሰጡት መግለጫ «በታላቅ ተስፋና ስሜት ወደ አብያተ ክርስቲያናት የበዓል ቀናት መቃረባችን ነው ብለዋል።

አብዛኞቹ የፊንላንድ ክርስቲያኖች የወንጌላዊት ሉተራን ቤተ ክርስቲያን አባላት ሲሆኑ የተቀሩት ምዕመናን ደግሞ ኦርቶዶክሶች የሮማ ካቶሊኮች ሜቶዲስቶችና ሳልቬሽን አርሚ (የደኅንነት ሠራዊት) አባላት ናቸው። እነዚህም የአብያተ ክርስቲያናቱ አንድነት ድርጅት አባሎች ሲሆኑ የሰባተኛው ቀን አክባሪዎች (አድቬንቲስቶችም) እና የስዊድን ቋንቋ ተናጋሪ ቤተ ክርስቲያን አባላትም በአንድነቱ ጉባዔ ውስጥ ተመልካች አላቸው ።

እንደዚሁም የፊንላንድ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ድርጅት ከፊላንድ ሉተራን ምዕመናን የሥራ ኅብረት ጋር አብሮ በመተባበር ይሠራል ብሎአል ።

✶ ✶ ✶

ኖርዌይ

በአሁኑ ጊዜ አሜሪካ እሠራለሁ እያለች ዓለምን የምታስፈራራበት ኒውትሮትን የተሰኘው ሌላው አደገኛ ቦምብ እንዳይሠራ ሰላም ወዳድ ድርጅቶችና ግለሰቦች በተቃውሞ ላይ ይገኛሉ ።

በዚሁ መሠረት የኖርዌይ ሊቀ ጳጳስ ይኸው ኒውትሮን የተሰኘ አደገኛ ቦምብ ተሠርቶ በሙከራ ላይ እንዳይውል ያለውን ተጽእኖ ሁሉ እንዲያደርግ መንግሥታቸውን ጠይቀዋል ።

ሊቀ ጳጳሱ ከዚሁ ጋር በማያያዝ የዚህ ጦር መሣሪያ መሠረት በዚህ ረገድ ያለውን ውድድር ያመለክታል ካሉ በኋላ ለዚህ መሣሪያ ቅድሚያ የሰጠውንና ከዚህ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለውን ኅብረተሰብ ተችተዋል ሲል የዓለም ሉተራን ፌዴራሲዮን የሚያዝያ መጽሔት አመልክቷል ።

★ ★ ★

ቦሊቪያ ፤

በደቡብ አሜሪካ በቦሊቪያ የተሰኘ



www.ethiopianorthodox.org

ችው አገር አዲስ ተሹዋሚ የሜቶዲስት ጳጳስ አገኘች ።

ኤኪውሚውኒካል የተሰኘው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መጽሔት በአገሪቱ ዋና ከተማ ባቀረበው ዜና በቦሊቪያ የምትገኘው የወንጌላዊት ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ዓመት ሥራውን በተሻለ ዘዴ ለመምራት ሲወያይ ከቆየ በኋላ ጳጳስ ዘካርያስ ማማኒ ሊያገለግሉት ተሹመዋል። እርሳቸውም ምዕመናኑን በማስተባበርና የቤተ ክርስቲያኒቱም ቋሚ ተጠሪ በመሆን ይሠራሉ ሲል በሚያዝያ ፲፱፻፸ ዓ·ም ቁጥር ፱/ ፵፩ መጽሔት አመልክቷል ።

## አሜሪካ ፤

በአሜሪካ የሚገኘወ የተባበሩት ፕሪስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያንና የሞስኮ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሀል ስለጋራ ፕሮጀክት ጉዳይ ውይይት እንደሚደረግ ታውቋል ።

ኤኩሚኒካል ፕሬስ መጽሔት እንደ ገለጠው ከሆነ ፤ ስለዚሁ ጉዳይ ለመነጋገር የ፲፰ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የሚገኙበት ቡድን ወደ ሞስኮ ሔዷል።ውይይቱም በሞስኮ በሌኒንግራድ በዘጉርስክ ፣ በቭላዲየር እና በኪይቭ በሚገኙ መንፈሳዊ መሪዎች መሀል ይደረጋል ። የመነጋገሪያ አርእስትም ፤ ስለወደፊቱ የአቢያተ ክርስቲያናት ግንኙነት በሁለቱ ኃያላን አገሮች ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ስላሉ ችግሮች ፤ በእምነት ይዘታቸው ላይ (የቲዎሎጂ) ውይይት እና በጋራ ሊያካሂዱት ስለሚችሉት ፕሮጀክት ወይም የሥራ እቅድ ይነጋገራሉ ።

ከዚሀ ቀደም እንደሚታወሰው ሁሉ በሩሲያ የቲኦሎጂ ምሑራንና በአሜሪካ የሚገኘው ማኮርሚክ ስሚናሩ ቺካጐ መሀል ከሁለት ዓመት በፊት ውይይት ተደርጐ ነበር ።

እንደዚሁም በ፲፱፻፸፱ ዓ·ም ከተባበሩት ፕሪስቢቴሪያን አብያተ ክርስቲያናት ስሚናሪዎች የቲኦሎጂ ተማሪዎች ወደ ሩሲያ ቲኦሎጂ ት/ቤቶች መጥተው የሃሳብ መለዋወጥ አድርገው ነበር ።

የዘንድሮዎቹ ልዑካን ደግሞ በመሪዎች ደረጃ ከተባበሩት ፕሪስቢቴሪያን አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ናቸው ። የዚህ ልዑካን አስተናጋጅ ሜትሮፖሊታን ፊቢናሲ ሲሆኑ እርሳቸውም በሞስኮ በሚገኘው መንበረ ፓትሪያርክ የውጭ ጉዳይ ክፍል ይሠራሉ ፤ ሲል ኤኩሚኒካል ፕሬስ መጽሔት አስታውቋል ።

★ ★ ★

## ሀንጋሪ ፤

በሀንጋሪ የመ/ቅዱስ ማኅበር ለመተርጐምና በእለተ ሰንበት ለሀንጋሪ ክርስቲያኖች ለማከፋፈል በመጣር ላይ ነው ማኅበሩ ፯ሺህ መጽሐፍ ቅዱስን በግማሽ ዋጋ መጠነኛ ገቢ ላላቸው ይሸጣል ። የታሰበውን ዓላማ ለማዳረስ ይችል ዘንድ ፵፩ሺህ፮፻ የኢትዮጵያ ብር ያስፈልጋል ። ከ፵ሺህ በላይ የሆኑ አዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለተሸጡ እንደገና ለማሳተም ፳፮ሺህ የኢትዮጵያ ብር ፳፱ ቶን የማተሚያ ወረቀት መግዣ ጠይቋል ሲል የተባበሩት የመ/ቅዱስ ማኅበር መጽሔት በ፯፰ኛው እትም ላይ ገልጿል ።

## ሩማንያ ፤

የሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በእስትሪያ ዋና ከተማ በቬና ለሚኖሩት ሮማንኛ ቋንቋ ለሚናገሩት ሮማንያውያን በሮማንኛ ቋንቋ የተጻፈ ፰ሺህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ እንዲላክላቸው የተባበሩትን የመ/ቅ/ ማኅበርን ጠየቀች ፤ የመጽሐፍቱም ዋጋ ፹፰ሺህ፮፻ የኢትዮጵያ ብር መድረሱ ታውቋል ። እንዲሁም ለ፩፻ሺህ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማሳተሚያ የሚሆን ወረቀትንና ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን የሮማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ጁስቲን መረከባቸውን ለተባበሩት የመ/ቅ/ ማኅበር ከምስጋና ጋር አስታውቋል ሲል የተባበሩት መ/ቅዱስ ማኅበር በግንቦት ወር ፲፱፻፸፭ ዓ·ም· ባወጣው እትሙ ላይ አስታውቋል ።

የሮማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለኦልቴንያ ሜትሮፖሊትና ለክራዩቫ ረዳት ጳጳስ ሁነው የሚያገለግሉትን ጳጳስ ኔስትር ቦርኒቸስኩን መረጠ። እርሳቸውም አሁን የተሾሙት በሜትሮፖሊት ቲዎክቲስት እግር መሆኑ ታውቋል ።

እኒህ ጳጳስ የድርሰት ባለሙያ እንደ መሆናቸው ሁሉ የሩማኒያን ባህል በሚመለከተው ረገድ እያሉ መጻሕፍትን ደርሰው አሳትመዋል ። ከዚህም በስተቀር በመንፈሳዊው ረገድ የጥንቱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሁር ናቸው ። እድሚያቸውም ፶፩ ሲሆን በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ በዓለም ታዋቂ አዛውንት ናቸው።ከዚሁ ጋር በተገኘው ዜና እንደተረጋገጠው ጳጳሱ በሩሜኒያ ፓትሪያርክ ስም በአብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ሁሉ ላይ ተጠሪ እንደሚሆኑ ታውቋል ሲል ኤኩሙኒካል መጽሔት በሚያዝያ ፲፱፻፸፭ እትም አስታውቋል ።



# የእግዚአብሔር ህላዌ

«አሪስቶትል» የተሰኘው ጥንታዊን የጽርዕ ፈላስፋ የእግዚአብሔርን መኖር በምሳሌ ሲያስተምር እንዲህ ይል ነበር ። «በደረቅ ምድር (የብስ) ላይ ሆኖ ከሩቅ አንድ መርከብ ወደደቡብ ሲያመራና ቀጥተኛውን መሥመር ተከትሎ ሲሄድ የሚመለከት ሰው ከቦታው ርቀት የተነሣ ለጊዜው የሚታየው መርከቡ ብቻ ቢመስልም በመርከቡ ውስጥ ተቀምጦ መርከቡን ወደ ተፈላጊው አቅጣጫ የሚመራ አንድ ሰው መኖሩን ያምናል ። እንደዚሁም የዓለሙን አስደናቂ ሥራ ስንመለከት እንደመርከቡ ምሳሌ እንዲህ አድርጎ ዓለምን አግምሮ የፈጠረ (የሠራ) አንድ አምላክ መኖሩን እንድናምን ያስገድደናል ።»

እዎ አንዳንድ ግለሰቦች እግዚአብሔርን በሰብአዊ አስተሳሰብና ፍልስፍና እንደአሳብ ቀመር ለማወቅ ማለትም ቢቻል በዓይናቸው አይተው በእጃቸው ዳስሰው ለመረዳት ፈልገው ይህ የማይሳካላቸው ከንቱ አመለካከት መሆኑን በመገንዘብ አለ ከማለቱ ይልቅ የለም ብሎ መካዱ የተሻለ ቢመስላቸውም ሐቅ አይሸፈንም ምንም ። ዓይነት አረም ቢጫንባት ዕውነት ጥሳ መውጣትዋ አይቀርም ። ስለዚህም የእግዚአብሔር ህላዌ ለዓለም ከፍተኛ የፍልስፍናም ሆነ የሳይንሣዊ ጥበብ በረከት ባስገኙ ሊቃውንት እምነተ ጠንካራነት እየተረጋገጠ በመሄዱ እነሆ ከመላው ዓለም ሊቃውንትና ሳይንቲስቶች መካከል በሚበልጠው ክፍል ተደግፎ በማይነቃነቅ መሠረት ላይ ታንጾአል ። የእግዚአብሔርን ህላዌ መካድ እንደተራማጅነት ያስቆጥራል ብለው የሚገምቱ ይኖሩ ይሆናል ። ሐቁ ግን ይህ አይደለም ስለምን ቢባል ከማያምኑት መካከል ብዙ ወላዋዮችና አድር ባዮች የመኖራቸውን ያህል ከአማኞች መካከል ደግሞ ብዙ ተራማጅ ኃይሎች መኖራቸው ታሪካዊም ሳይንሣዊም ሐቅ ነው ። ተራማጅነት የሚለካው በተግባር እንጂ በማመንና ባለማመን አይደለምና ነው ።

ስለዚህ ነው የኪዩቫው አብዮተኛ መሪ «ማንም ግለሰብ የርእዮተ ዓለምን (የአይዲዮሎጂን) ልዩነት ወደጐን አድርጎ በማኅበራዊ ኑሮ በኢኮኖሚና በፖለቲካ አዝማሚያ ላይ ካተኰረ አማኝም አብዮተኛ ሊሆን ይችላል» ሲሉ የተናገሩት የዚህ አብዮተኛ የቅርብ ጓደኛ የነበረው ቼ ጉቤራም ሲመሰክር «የሃይማኖት ሰዎች ተባብረው አብዮት ቢጀምሩ በላቲን አሜሪካ የማይበገር ኃይል ሊፈጠር ይችላል» ብሏል ። ይህም አባባል በእግዚአብሔር ህላዌ ማመን ማንንም ሰው ቢሆን አብዮታዊ አስተዋጽኦ ከማድረግ ወደኋላ እንደማይገታው በግልጥ ያመለክታል። ይኸው ሰው እንደገና ሲናገር»አንድን ሰው ለአብዮተኛነት የሚያነሣሣው ራሱ ፍቅር ነው» ብሏል ። ያም ሆነ ይህ ማንም ይመን ወይም ይካድ እግዚአብሔር ራሱን ያለምስክርነት ያልተወ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው ። ይህንም አስቀድሞ በፍጥረቱ መዝ·፲፰፥ ፩ ሮሜ ፩ ፥ ፲፱—፳፩ ቀጥሎም በነቢያት ዕብ· ፲፩ ዘኁ ፲፪ ፥ ፮-፰ እንዲሁም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ዕብ ፩ ፥ ፩—፪ ገልጦአል ። እርሱ የማይለወጥና የማይታይ አምላክ ነው ። ሚል ፫ ፥ ፮ ። ፩ኛ ጢሞ ፮·፲፮ አካላዊ መንፈስ ነው ዮሐ ፬ ፥ ፳፬ ከርሱ በፊት ምንም ያልነበረ የሁሉ መገኛ አምላክ ነው ኢሳ· ፵፫ ፥ ፲—፲፰ ።

( ይቀጥላል )

መክብብ አጥናው

# ልማድ ሃይማኖት አይደለም

ልማድ ሲባል ብዙ ዓይነት ልማድ አለ ይኸውም ጥሩ ልማድ አለ መጥፎ ልማድ አለ ።

መጥፎ ልማድ እምነትን ኅብረተሰብን ሲጐዳ ጥሩ ልማድ ደግሞ የአንድ ሀገር ኅብረተሰብን መንፈስ የሚያስተሳስርና ስሜትን የሚቀሰቅስ የኑሮ ዋስትና ነው ሊባል ይቻላል ። በእምነት በኩል ደግሞ የሕይወት መተላለፊያ የሆነውን ተግባር በሥራ እንዲውል የሚያጎርግ ነው ። ይህ ብቻ አይደለም ልማድ የአገርን ወግና መአርግ ይዞ ሲጓዝ መጥፎውንና የጥንቱን አጉል ልማድ እያረመ የሚሄድበት ወቅት አለው ። ከዚህም የተነሳ ጥሩ ልማድ እንደ እርሾ ጀግንነትን ፤ ድፍረትን ፤ እውቀትን ፤ በሕዝብ ልብ ስለሚያቦካ ጣፋጭ ኅብስተ መና ነው ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ ልማድ ከሃይማኖት ጋር እየተጣመረ ይመጣና ከጊዜ ብዛት ልማዱን ከሃይማኖት ለመየት የሚያስቸግርበት ጊዜ አለ ። ያም ሆኖ ልማድ ዓይነቱ በዝቶ ጥሩና መጥፎ ሲኖረው ሃይማኖት ግን ሁልጊዜ ወደ ጥሩ መንገድ የሚመራ ብርሃን ነው ልንል እንችላለን ።

ፈላስፋው ሆኪንግ ይህንን በማስመልከት ሲናገር«የዓለም አቀፍ ሕግ መንገድ ጠራጊ ሃይማኖት ነው ምክንያቱም ዓለም አቀፍ መንፈስንና ግዴታን ሊፈጥር የሚችል እርሱ ብቻ ስለ ሆነ ነው» ብሏል ።

እዎን ሃይማኖት የዓለም አቀፍ ሕግ መንገድ ጠራጊ ነው ። ሃይማኖት ስለ ወገን ፍቅር፣ስለ ሰው ልጆች እኩልነትና አንድነት፣ስለ ሰላም በጠቅላላው ስለ ጥሩ ስነ ምግባር የሚያንጸባርቅ ወይም የሚመራ ጉዳና እንጅ እንደመጥ



www.ethiopianorthodox.org

ፎ ሥነ ሥርዓት ጭቆናን የሚያስተምር አይደለም ። ይህም የሚታወቀው በአጉል ልማዶች ተተብትበው በሚራመዱ አጉል ሃይማኖታውያን ነን ባዮች ሳይሆን ከእውነተኛ ሃይማኖታውያን ትምህርቱንና ዓላማውን በግልጽ በሥራቸው ልንረዳ እንችላለን ። ምክንያቱም ራሱ ሥራቸው አፍ አውጥቶ ይናገራልና ሃይማኖት በኅብረት መሥራትን በኅብረት መጸለይን ይፈቅዳል ። ይኸውም ኅብረት የሥራ መድኃኒት፣ ኅብረት የመልካም ኑሮ ምልክት፣ኅብረት የሰው ልጅ ኃይል ናት ብሎ ስለሚያምን ነው ።

ነገር ግን በጣም ብዙ የሆኑ ሰው ሰራሽ መጥፎ ልማዶች ከጊዜ መርዘም የተነሳ እየተለወጡ ከሃይማኖት ጋር ይጣመሩና እነዚያ ልማዶች ከመቆየት የተነሣ ራሳቸው ሃይማኖት ሆነው ቁጭ ይላሉ ። በዚህ ምክንያት በጎውና መንፈሳዊው የበዓላት አከባበር ዓላማቸውን ለቀው ከእውነት ርቀው እንደ ሟርት ሆነው ቆሌ ፤ አድባር ውቃቢ ብለው እየሰየሙ ወደ አምልኮተ ጣኦት ይለውጡታል ለምሳሌም የግንቦት ልደታ ፤ የቅዱስ ዮሐንስ በዓል ፤ የመስቀልና የመሳሰሉትም ሲሆኑ በነዚህ ዕለታት ንፍሮ ከውጭ ሲያነፍሩ ቂጣ በቅቤና በበርበሬ ሲቀቡ፣ ደም ሲያፈሱ፣ስብ ሲያጤሱ ይውላሉ።በዚያን ዕለት ለእቴቴ ለአድባር ግብር ያልከፈለ ይታመማል እያሉ የልማድ ተገገርዎች ሲያወሩ ስለ ሃይማኖታቸው ያላወቁና ያልተረዱትም የሃይማኖት ግዴታ እየመሰላቸው በየቤታቸውና በየ መንደራቸው ሲፈጽሙት ይታያሉ ።

እንደነዚህ ላሉት ተምረው ወይም ተነግሯቸው ከስህተታቸው ለማይመለሱት የአጉል ልማድ ተገገርዎች ለሆኑት ሰዎች ፈላስፋው ቦልቴር ሲናገር «የማመዛዘን ኃይላቸው በደከመ ኅሊናቸው በደነዘዘ ሰዎች ዘንድ የሃይማኖት እውነተኛነት በደንብ አይታወቅም» ሲል ተናግሯል ።

እንግዲህ እንዲህ ከሆነ ዘንድ በአሁኑ ጊዜ በደንብ የተመለከትን እንደሆን አጉል ልማዶች ከሃይማኖት ጋር ተጣምረው ስለሚራመዱ በወጣቱ ትውልድ ዘንድ ሃይማኖትን ሲያስነቅፉ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ያህል በአገር ቤትና በከተማም በአንዳንድ ቦታ ሴቷ ወጥታ ወርዳ ያዘጋጀችውን ወይም የጋገረችውን ዳቦ ራሷ አትቆርሰውም ወንዱ ተጠብቆ ሲመጣ እርሱ ከቆረሰ በኋላ ታከፋፍላለች እንጂ ዳቦውን ለመቁረስ ምንም ሥልጣን የላትም ። እንግዲህ እንባብያን ራሷ የጋገረችውን ዳቦ እንድትባርክ ያልተፈቀደላት ዶሮና በግ ራሴ ልባርክ ብላ ብትጠይቅ ማን ይፈቅድላታል ? ይህ አጉል ልማድ እንጂ ሃይማኖት ነው ይሉት ይሆን ? መልሱን ለናንተው እተወዋለሁ ።

ከዚህስ ሌላ እንጀራ መጋገር ወጥ መሥራት የሴት ሥራ ነው ። ማረስ የወንዱ መጕልጐል የሴቷ ብሎ የደነገገውስ የትኛው ሃይማኖት ነው ? አሁንም በሰዎች ዘንድ የሚነፍሰው ወሬ ይህ ሃይማኖት ነው ፤ ሴቶችን የሚጨቁነው እየተባለ ይተቻል ። «ሰዎች የተፈጠሩት እንዲረዳዱና የኑሮን ቀንበር አብረው እንዲሸከሙ ነው» ብሎ ፈላስፋው ማርከስ ኦሬሊያስ የተናገረውን ሃይማኖት የሚያሳምንና የሚያስተምር እንጂ አንዱን ወገን ብቻ የሚደግፍ ሌላውን የሚያኳስስ አለመሆኑን ለማወቅ መዝሙረኛው ዳዊት መዝ - ፴፫ ቁ-፰ «እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነው» ። ይላል ። አዎን የአንድን ነገር ጣእም የሚያውቀው ያ የቀመሰው ስለሆነ ቅረቡና ቅመሱት ከዚያ በኋላ ሃይማኖት የጥሩ ሥራና የእኩልነት መሪ መሆኑን ለማወቅ ትችላላችሁ ።

በትምህርት በኩል የተመለከትን እንደሆን ብዙ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተማሩ እናቶች አሉ እነዚህም ሴቶች ቅኔ ፤ ድጓ ቅዳሴ የመሳሰሉትን የተማሩ ሲሆኑ በዚህ ሞያቸው በመምህራንነት ደረጃ በማገልገል ላይ ይገኛሉ ቢሆንም ለስሙ ሞያቸው መምህራት ሲሆኑ የደቀ መዛሙርታቸውን ያህል ሥልጣን የላቸውም ቤተ ክርስቲያን ገብተው ቅኔ ማኅሌት ቋመው ከወንዶቹ ጋር በእውቀታቸው ሊቀኙ፤ ሊዘምሩ ፤ ሊያዜሙ አይችሉም ። ለምሆን እነርሱ ገብተው ቢቆሙ ለቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነ ለአበው ሊቃውንት ምን ጉዳት ያደርሳሉ?ይህ አጉል ልማድ እንጂ የትኛው የሃይማኖት ሕግ ነው እንዳይገቡ የሚከለክል ? ምንምየለም።

የሆነ ሁኖ ኅብረተ ሰቡ ሃይማኖትን ሰበብ በማድረግ ልዩ ልዩ የጭቆና ልማዶች በሴቶች ላይ ሲፈጸም ኖሯል ። አሁንም በአንዳንድ ቦታ በመፈጸም ላይ ነው ።

ስለዚህ ሃይማኖት ስለ ሃይማኖትነቱ ብቻ ሳይሆን ለማኅበራዊ ኑሮም እድገትና ሥልጣኔ የሚያበረክተው አገልግሎት ዋጋ እንዳለው ታስቦ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲደረግበት የሚያስፈልግ መሆኑን ለሚመለከተው ሁሉ እንጠቁማለን። ካልሆነ ግን ሳይመራመሩ ፤ ሳይወጡ ሳይወርዱ ሃይማኖትን መስለው የሚገኙትን መጥፎ ልማዶች መቀበል ትልቅ ስህተት ነው ካልታሰበበት አደጋ ላይም ይጥላል ። ስለሆነም ልማድና ሃይማኖት በጣምራ ሃይማኖት ተብለው እየተጠሩ ሊነቀፉና ሊመሰገኑ አይገባቸውም ሁሉም በየሥራው ሊመሰገን ይገባዋል እንጂ የትኛው ክፍል ልማድ የትኛው ክፍል ሃይማኖት መሆኑን ኅብረተሰቡ ለይቶ ማወቅና መረዳት አለበት እንዲያው በደፈናው « በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደሰ»እንደሚባለው ልማድ በሃይማኖት አማካኝነት እንዲመሰገን ወይም ሃይማኖት በልማድ አማካኝቶ እንዲወቀስና እንዲከሰስ ለማየትና ለመስማት አንሻም ምክንያቱም ልማድ ሃይማኖት አይደለምና ።

ብርሃን ተድላ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ዶ

## ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስተምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ስለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቁ 11፥፥፥
የመል ሣ 31፥
አዲስ አበባ ።

www.ethiopianorthodox.org